ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

አሰጋሽ ዘለቀ

ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ታህሳስ 2014 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

አሰጋሽ ዘለቀ

ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

የጥናቱ አማካሪዎች

ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)

ደመላሽ መንግስቱ (ዶ/ር)

ታህሳስ 2014 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

# በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

አሰጋሽ ዘለቀ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አማካሪ | ________________ | ፊርማ | ________ |
| ፈታኝ | ________________ | ፊርማ | ________ |
| ፈታኝ | ________________ | ፊርማ | ------------ |

# ማረጋገጫ

በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለኤም ኤ.ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛዉም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸዉ ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለዉ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-----------------------------------------

ፊርማ----------------------------------------

ቀን-------------------------------------

# ምስጋና

አሁን ያለንበት ወቅት እጅግ ፈታኝና ከአቅም በላይ የሆነ ምጥ እንደ ያዛት ሴት የሚያንገበግብ ቢሆንም በእነዚህ በማይመቹ ሁኔታዎች መካከል በረቂቀ ጥበቡ ለረዳኝ ልዑል እግዚአብሄር ምስጋናዬ ወደር የለዉም፡፡በመቀጠልም የተለያዩ ሙያዊ አስተያየታቸዉን እየሰጡኝ ለረዱኝ አማካሪዎች ዶ/ር ምህረት ሳዳም እና ዶ/ር ደመላሽ መንግስቱ ምስጋናዬ ይድረሳቸዉ፡፡ ድርሰቱን በመፃፍና የፅሁፍ መጠይቁን በመሙላት ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ የኩቢጦ 2ኛ ደረጃ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እና የቃለ መጠይቁን በመሙላት አስፈላጊዉ መረጃ እንድሰበሰብ የተባበሩኝን የአማርኛ ቋንቋ መምህራንንም ሳላመሰግን አላልፍም፡፡

# የይዘት ማዉጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና ........ i
የይዘት ማዉጫ ........ ii
የሠንጠረዥ ማዉጫ ........ v
አጠቃሎ... ........ vi
ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ ........ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 4
1.4. የጥናቱ ዓላማ ........ 4
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7. የጥናቱ ዉስንነት ........ 5
ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........ 6
2.1.1. የስህተት ምንነት ........ 6
2.1.2. የስህተት ምንጮች ........ 8
2.1.2.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ........ 9
2.1.2.2. የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ........ 10
2.1.2.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት 11
2.1.2.4. ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ........ 13
2.1.3. የስህተት ትንተና ዘዴዎች ........ 14
2.1.3.1. የስነ ልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ........ 14
2.1.3.2.የዐረፍተ ነገር ቅርጾችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ........ 14
2.1.3.3.ንጽጽራዊ ክፍፍል ........ 15
2.1.3.4.ተግባቦታዊ ተጽእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ........ 15

2.1.4. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ ........ 17
2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 19
ምዕራፍ ሦስት፤የአጠናን ዘዴ እና ንድፍ........ 23
3.1 የአጠናን ዘዴ ........ 23
3.2. የጥናቱ ንድፍ ........ 23
3.3. የናሙና አመራረጥ ........ 23
3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ........ 23
3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 24
3.4.1. ድርሰቶች ........ 24
3.4.1.1 የድርሰት መልመጃዎች አተናተን ........ 25
3.4.2 መጠይቆች........ 26
3.4.2.1 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ........ 26
3.4.2.2 የመምህራን ቃለ መጠይቅ........ 26
3.5. የመረጃ አተናተን ........ 26
3.5.1 የመጠይቆች አተናተን........ 27
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ........ 28
4.1. የመረጃ ትንተና ........ 28
4.1.1 በድርሰቶቹ ዉስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተት ብዛት........ 28
4.1.2 በድርሰቶቹ ዉስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች ........ 29
4.1.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ........ 31
4.1.2.1.1 ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ያለመጠቀም........ 33
4.1.2.1.2 በቃላት አመራረጥ ምክንያት የታዩ ስህተቶች ........ 35
4.1.2.1.3 በግድፈት ምክንያት የተስተዋሉ ስህተቶች........ 37
4.1.2.1.4 የቃላት ድግግሞሽ........ 38

4.1.2.1.5. የቃላት ጭመራ(እከላ) .................... 39

4.1.2.2. የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች .................... 41

_4.1.2.2.1 የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት .................... 43

4.1.2.2.2. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት .................... 44

4.1.2.2.3 የድርብ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት .................... 45

4.1.2.2.4 . የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት .................... 47

4.1.2.2.5 የሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተት .................... 48

4.1.2.3. በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋሰዉ )ስር የታዩ ንዑሳን ስህተቶች .................... 49

4.1.2.3.1 የዓረፍተ ነገር ስሙምነት አለመኖር .................... 51

4.1.2.3.2 የቃላት አጠቃቀም ስህተት .................... 53

4.1.2.3.3 የመስተዋድድ እናየተሳቢ አገባብ ስህተት .................... 54

4.2. የስህተት ምንጭ መላምቶች .................... 56

4.2.1. የዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ .................... 56

4.2.2.የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ .................... 61

4.2.3.የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት .................... 64

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት .................... 70

5.1. ማጠቃለያ .................... 70

5.2. አስተያየት .................... 73

ዋቢ ፅሁፎች .................... 74

አባሪዎች

## የሠንጠረዥ ማዉጫ


ሠንጠረዥ 1.ድርሰቶቹ የተጻፉባቸዉ ቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛት በመቶኛ ወዘተ መግለጫ……………………………………………………………………………28

ሠንጠረዥ 2. በተማሪዎቹ ድርሰት ዉስጥ የተገኙ የስህተት ዓይነቶች ከስህተት ብዛት፣ ከስህተት ብዛት በመቶኛ ወዘተ መግለጫ…………………………………..30

ሠንጠረዥ 3- በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ዉስጥ የተፈጸሙ ስህተቶች ………...32

*ሠንጠረዥ* 4 በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ የተፈጸሙ የስህተት ዓይነቶች ………….42

ሠንጠረዥ 5 በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ዉስጥ የተገኙ የስህተት ዓይነቶች ......50

ሠንጠረዥ 6. አናባቢ / ኧ/ና / እ / በሽክኛ ቋንቋ ዉስጥ ባለመኖራቸዉ በተጠኚ ተማሪዎቹ የቃላት አጻጻፍ ላይ የተስተዋሉ ስህተቶች ………………………………63

ሠንጠረዥ7.የመማር ማስተማር ሂደትና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በተመለከተ ተማሪዎች የቀረበላቸዉ ጥያቄዎች……………………………………………………..…63

ሠንጠረዥ 8 የመማር ማስተማር ሂደትና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አዘገጃጀት በተመለከተ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ…………………….………….65

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሽክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች መለየትና ለስህተቶቹ መፈጸም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነዉ። ጥናቱም በረድፋዊ ናሙና ዘዴ 40 ተማሪዎችን አካቷል። ለጥናቱም አስፈላጊዉን መረጃ ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ዙር 64 ድርሰቶች ተጽፈዋል ።በተጨማሪም ተማሪዎቹ የጽሁፍ መጠይቆችን ሲሞሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ደግሞ የቃለ መጠይቆችን ሞልተዋል።በዚሁም መሰረት ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ የፈጸሟቸዉ ስህተቶች ታዉቀዋል ።ይኸዉም ጠቅላላ የስህተት ብዛት 1498 ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ የቋንቋ አጠቃቀም 941፣የቋንቋ አወቃቀር 174፣የስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም 353 መሆኑ ታዉቋል። ተማሪዎቹ ከጻፉት ድርሰቶችና ከሞሉት የጽሁፍ መጠይቆች እንዲሁም መምህራን ከሞሉት ቃለ መጠይቅ በመነሳት የስህተት ምንጮች ተገምተዋል። እነርሱም የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ እና የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ክፍተት ናቸዉ።በጥናቱ ዉጠት ላይ በመመርኮዝም ከአፍ መፍቻ ቋንቋና ዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊታደጉ የሚችሉ መልመጃዎች ትኩረት ቢሰጣቸዉ የተሻለ ይሆናል።ተማሪዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሀሳብ ሰብስቦ በመፃፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች የማቅረብ ልምድ እንድኖራቸዉ ቢደረግም ይመረጣል።በተጨማሪም የፅህፈት ማለማመጃዎቹ ከድምፆች አሰዳደር፣ከቃላት፣ከሀረጋትና ዐረፍተ ነገሮች አቀነጃጀት ጋር የሥርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም አፅንኦት ቢሰጡ ስህተቶችንና ምንጮቻቸዉን መቀነስ ይቻል ይሆናል የሚሉ መፍትሄዎች ተገምተዋል።*

# ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የጽህፈት ክሂል ከአራቱ የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ክሂል እንደ ማዳመጥ እና መናገር ክሂሎች ለቋንቋው ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚለመድ ሳይሆን አፍ ፈቶችም ሆኑ ኢ-አፍ ፈቶች በመደበኛ ትምህርት እገዛ በሚያደርጓቸዉ ተደጋጋሚ ልምምዶች የሚዳብር ነዉ፡በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ጽህፈትን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለጽ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ እና ማህበራዊ አጠቃቀም ጭምር ማወቅን ይፈልጋል(Ring Born፣1992፣Brown፣1994)::

መፃፍ በአንድ በተወሰነ ልማዳዊ ስርዓት በእይታዊ ትዕምርቶች ስምረት ቃልን ከቃል፣ ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽን ከአንቀጽ ወዘተ በማቀናጀት የቋንቋ ስርዓተ አፃፃፍን ተከትሎ አንድ ውስን የሆነ ቅርጽ የሚያስገኝ ተግባር ነው፡፡ በጥቅሉ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚፈጥሩበት ተግባቦታዊ የቋንቋ መሳሪያ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ Byrne (1990:14) እንዳብራሩት መፃፍ በትዕምርቶች የመወከል ሂደት ብቻ ሳይሆን የአዕምሮንና የአካል እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት ይዘትን፣የአፃፃፍ ስልትን፣የአወቃቀር ስርዓትን፣የቃላት ምርጫን፣የሀሳብ ፍሰትን፣ ወዘተ. ያሉ በርካታ ባህሪያቱን ቅጽበታዊ በሆነ የመፃፍ ሂደት ውስጥ በመጠቀም የሚከናወን የአእምሮ ስራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መፃፍ በቂ ዝግጅትንና መማርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ማንኛውም በአካልና በአእምሮ ጤነኛ የሆነ ሰው በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር የሚችል ሲሆን ነገር ግን በቋንቋው እንዴት መፃፍ እንዳለበት፣ መማር አለበት (Nunan 1999:36) በሌላ በኩል መፃፍ ጊዜ ሰጥቶ በተከታታይ ልምምድን የሚጠይቅ የክሂል ዘርፍ መሆኑን Ur (1996: 26)፣Richards (1990:101) ገልጸዋል፡፡ የምሁራኑን ሀሳብ በማጠናከርም ዓለም (1995፡14) የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ መፃፍ ሀሳብን በትክክል ለማስተላለፍ ድምጾችን፣ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን በቋንቋ ስርዓት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበት ነው፡፡ አንባቢም መልዕክቱን በትክክል የሚገነዘበው የቋንቋን ስርዓት የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ መፃፍን አስመልክቶ ከቀረቡ አስተያየቶች መገንዘብ የሚቻለው የመፃፍ ክሂል አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት፣ ድምጾችን በምልክቶች በመመሰል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ሂደት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ተነድፎለት ከመጣበት ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ የአማርኛ የድርሰት ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ለመሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር (1970) የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በአማርኛ ዋና ቡድን ከተዘጋጁ ጽሁፎች መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ አቀናብረው መልዕክት ለማስተላለፍ የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑ በስፋት ይነገራል። ይህንኑ የጽህፈት ችግር በማመልከት ባየ (1987) ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የቋንቋ ትምህርት በሰዋሰው ላይ ያተኮረ እንደነበረና በአሁን ጊዜ ደግሞ በክሂል ዘርፎች ላይ እንዳተኮረ ገልጸው ሆኖም ግን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት በሚታይበት ጊዜ እንኳንስ ትምህርታቸውን ያልጨረሱት ቀርቶ አስራ ሁለተኛን ያጠናቀቁትም ቢሆኑ ሌላው ቢቀር የማመልከቻ ደብዳቤ መፃፍ እማይችሉበት ደረጃ እንደደረሱና ተማሪዎቹ ከቋንቋው ስርዓትም ሆነ ከክሂሉ እንደሌሉበት ያስረዳሉ።

ተማሪዎች በንግግራቸዉ ወይም በጽሁፋቸዉ ዉሰጥ ሰለሚፈጥሯቸዉ ስህተቶች እነ Dulay (1982) ቋንቋን በመልመድ ወይም በመማር ሂደት ስህተት መፈጸም አንዱ የመማር ተግባር ነዉ፤ ቢባልም ይህ የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት መጠናት የለበትም የሚል አንድምታ የለዉም።እንዲያዉም እነ Corder (1981)፣Littlewood (1984) እና Richards(1990) እንደሚገልጹት የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶችን ማጥናትና የስህተቶችን ምንጭ መለየት ለብዙ አካላት ጠቀሜታዉ የጎላ መሆኑን ይገልጻሉ።

በድርሰት ስህተት ትንተና ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚያስረዱት የተማሪዎችን ስህተት መረዳት፤ተማሪዎች በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸዉ የደረሱበትን ደረጃ ለመገንዘብ ይጠቅማል።ስለዚህም የድርሰት ስህተት ትንተና ለተማሪዎች ምን ዓይነት ምጋቤ ምላሽ መስጠት እንደሚገባ ይጠቁማል።Richards (1974) እና Dulay et al.(1982) እንደገለጹት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ስህተት እንደሰሩ ማወቃቸዉ ይጠቅማቸዋል እንጂ አይጎዳቸዉም።ስህተት መቼ ይሰራል?ለምን ይሰራል ? እንዴት ማስወገድ ይቻላል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ የስህተትን ምንጭ ለማድረቅ ካልተቻለም ለመቀነስ ይረዳል።

በተመሳሳይ Corder (1967)፣Edge (1989) እና Richards (1974) ጨምረዉ እንደገለጹት፤ ተማሪዎች ከሚፈጽሙት ስህተት በመነሳት ትንተና መስጠት ከተቀየሰዉ የትምህርት ግብ አንፃር ተማሪዉ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ፤ምን እንደቀረዉ እና ምን እንደሚያስፈልገዉ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።Candien (1979) ደግሞ እንደሚሉት የስህተት ትንተና የጥናት ግብ ከጥናቱ በሚገኙ መረጃዎች በመመርኮዝ የቋንቋ መማር ማስተማር

ችግርን ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመተለም የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ማሳካት ነዉ፡፡

በጽሁፍ የሚተላለፍ መልዕክትን አስመልክቶ Widdowson (1976፣118) በጽሁፍ የሚገለጽ ሀሳብ በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለአንባቢ ሊተላለፍ የሚችለዉ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ሲጻፍ ብቻ ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሀሳብ የሚያስረዳዉ በጽሁፍ መልዕክት ሲተላለፍ ዓረፍተ ነገሮቹ በጥንቃቄ መዋቀር እንደሚገባቸዉ ነዉ፡፡በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በስህተት ትንተና ላይ ከተደረጉ ጥናቶች ዉስጥ ለምሳሌ፡-መሰረት (2003) "በሀረማያ እና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸዉ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና" ፣የአምላክስራ (2008) "የአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ፅሁፍ ላይ የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና፣ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› የሚሉትን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በአማርኛ ጽህፈት ላይ ለሚታዩት ስህተቶችና የስህተት ምንጮች በዋና ምክንያትነት ያስቀመጡትም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖና የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የቀረቡትንና መሰል ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቶችን ከግምት በማስገባት ይህ ጥናት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና ላይ ያተኩራል፡፡

## 1.2. አነሳሽ ምክንያት

በጽህፈት ክሂል ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ አብዛኞቹ ጥናቶች ተማሪዎች በተለያዩ ሀገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን ፈተው በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች የቃኙ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት በአጥኚዋ ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎችም በንግግርም ሆነ በጽህፈት ከተለያዩ ችግሮች ነፃ አለመሆናቸውን መገንዘብ የመጀመሪያዉ ምክንያት ሲሆን በተጨማሪም አብዛኞቹ ተማሪዎች በንግግርም ሆነ በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች የሚያጠነጥኑት ተቀራራቢነት ባለዉ ቅርጽ ዙሪያ መሆኑ ለምን ይሆን? የሚለዉን የአጥኚዋን የአዕምሮ ጥያቄ በጥናት ያረጋገጠ ፈልጋ ማግኘት ስላልቻለች ይህንን ሁኔታ በጥናት ለማረጋገጥ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ለማጥናት አቅዳለች፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፡-

ሀ. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ለእነዚህ ስህተቶች መከሰት የስህተት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሽክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መለየትና ለስህተቶቹ መፈጸም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነው፡፡ ከዚህ አብይ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን የስህተት ዓይነቶች መለየት፡፡

- ለስህተቶቹ መከሰት የስህተት ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ማሳየት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የተማሪዎችን የጽሁፍ ስህተቶች ማጥናት ተማሪዎቹ ትምህርት የሚቀስሙበትን ብልሀት መገንዘብ እንደሆነ Corder (1967) እና Littlewood (1986) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ቀጥሎ የተገለጹትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች የሽክኛ ቋንቋ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ሊፈጽሙ ለሚችሉት የድርሰት አፃፃፍ ስህተቶች ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አስቀድመው እንድጠቁሙ ያስችላቸዋል፡፡

- ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም የሽክኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸዉን ስህተቶች መቅረፍ የሚችሉበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡

- በዚህ ርዕስ ዙሪያ ወደፊት ሰፊ ጥናት ለሚያካሂዱት አጥኚዎች እንደ መነሻ ሀሳብ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በወረዳዉ ከሚገኙት አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል የሸክኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸዉን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ይለያል፡፡ የተማሪዎቹን ስህተት በመተንተን ሂደትም የሆሄያት አሰዳደርን፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን፣የቃላት፣የሐረጋት እና የዐረፍተ ነገሮች አወቃቀር ትክክለኛነትን የሚመረምር ሲሆን ከዐረፍተ ነገር በላይ የሆኑ ጽሁፋዊ ይዘቶች የዚህ ጥናት ትኩረት አይሆኑም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዉስንነት

ይህ ጥናት በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ኩቢጦ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትን በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የመረጠ ቢሆንም በአንፃሩ በአንድ ትምህርት ቤትና በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ የተከናወነ ጥናት ነዉ፡፡ይህም በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች ዓይነትና ምንጮቻቸዉን ተጨባጭ ወይም የመጨረሻ ሊባል የሚችል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አያስችልም ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1. የስህተት ምንነት

የአፍ መፍቻንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ ስህተቶችን እንፈጽማለን፣ ከተፈፀሙት ስህተቶች በመማርም ቋንቋን እንለምዳለን በማለት Dulay (1982:138), Brown (1994, 254-255) ይገልፃሉ። ከዚህ ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለዉ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ወቅት ስህተቶች ይፈፀማሉ፤ ይሁን እንጂ ስህተቶቹን ለማሻሻል የምናደርጋቸዉ ጥረቶች በራሳቸዉ ቋንቋን እንድንለምድ ማስተማሪያ መሆናቸዉ ነዉ።

አብዛኞቹ ምሁራን ስህተት የሚፈጸመው በተማሪዎች ድክመት እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሲሆን ይህም ትምህርቱ በሚሰጥበት ጊዜ በሚገባ ካለማዳመጥ ለትምህርት ምንም ዓይነት ትኩረት ካለመስጠት ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ወይም ደግሞ ለተማሪዎቹ በቂ የልምምድ ጊዜ ካለመስጠት የተነሳ የተከሰተ ነው የሚል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ግድፈትን ስህተት መፈጸምን በትክክል የትምህርቱ የመጀመሪያ አካል እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። በመሆኑም ስህተት የድክመት ምልክት ተደርጎ መታየት የሚገባው ሳይሆን የተማሪው የቋንቋ ለመዳ ስርዓታዊ እድገትና ተማሪዎች ቋንቋውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለው ሂደት እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚፈጽሙት ስህተቶች እንደ ጉድለት በሚቆጠሩና መወገድ ያለባቸው መሆኑንም በሚያምኑት ዘንድ ተማሪዎች ስህተት መፈጸማቸው በመምህሩም ሆነ በተማሪውም ተግሳጽና ቁጣን ያስከትልባቸው እንደነበር Littlewood (1986:225), Norrish (1992:1) ይገልፃሉ።

ከዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ግድፈትን ወይም ስህተትን ለመፈጸም ይፈራሉ። የፍራሃታቸው ምንጭም ተማሪዎቹ ግድፈት ወይም ስህተት በሚፈጽሙበት ጊዜ በቋንቋው አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች እንዲሁም በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸው ይሳቅብናል ከሚል ፍርሃት የተነሳ በትምህርቱና በተማሪዎቹ ላይ ጥላቻ ያድርገባቸዋል በማለት Norrish, (1992:1) ይገልፃሉ። ከላይ የቀረበዉ ሀሳብ የሚያስረዳዉ ስህተት የሚፈፀመዉ ተማሪዎቹ በትምህርት ወቅት ትኩረት ካለመስጠታቸዉ እና ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት የተነሳ ነዉ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ስህተት መፈፀምን የድክመት ምልክት ሳይሆን

ተማሪዎች ቋንቋዉን በሚጠቀሙበት ጊዜ ቋንቋ ለመዳ ስርዓታዊ እድገት እና ቋንቋዉን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለዉን ሂደት ያመለክታሉ፡፡ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ለሚፈፅሙት ስህተቶች ስህተት መፈፀማቸዉ ስለሚያሳፍራቸዉ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት እንደሚያሳድርባቸዉም ይገልፃል፡፡

በሌላ በኩል Negara (1983:35-36) እንዳስቀመጡት ስህተትን የአፈጻጸም ችግር ስህተት (Performance error) እና የብቃት ማነስ ስህተት (competence error) ብለን በሁለት መክፈል እንችላለን ይላሉ፡፡ ይህዉም የአፈፃፀም ችግር ስህተት የሚንለው ግድፈትን ሲሆን ይህም ማዳጥ፣የተወሰኑ ቃላት ወይም የሆሄያት ግድፈትን፣ድግግሞሽን ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ ተማሪው እነዚህን ስህተቶች የሚፈጽመው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በችኮላ፣ በስሜት ወይም ጭንቀት ውስጥ ሆኖ በመናገር ወይም በመፃፍ አሊያም በግዴለሽነት ነው፡፡ እነዚህን ግድፈቶች አፍ ፈቶችም ሆኑ ኢ-አፈ ፈት ተናጋሪዎች ሊፈጽሟቸው ስለሚችሉ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ቋንቋ ምን ያህል እንዳዳበሩ ሊገልጹ አይችሉም፡፡ የብቃት ማነስ ስህተት የምንለው ደግሞ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ላይ ያላቸውን ብቃት የሚያመለክተውን ነው፡፡ እነዚህም ስህተቶች በትክክል የተማሪውን ስህተት የሚያሳዩ ሲሆን ተማሪ በታላሚው ቋንቋ የት ቦታ ችግር (ጉድለት) እንዳለበት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ግድፈትን ወይም የአፈፃፀም ችግር ስህተትን ለትክክለኛነቱ በጥንቃቄ ትኩረት በማድረግ መቀነስ ሲቻል የብቃት ማነስ ስህተትን መቀነስ የሚቻለው ግን ለታላሚው ቋንቋ ትምህርት ትኩረት በመስጠት እንደሆነ እኚሁ ምሁር ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም Brown (1994:205-206) ስህተትን ሲገልፁ ግድፈትና ስህተት በማለት በሁለት ከፍለው ይመለከቱታል፡፡ ምሁሩ የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ በተገቢ ሁኔታ መተንተን ካስፈለገ በስህተትና ግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ማጤን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፡፡ ግድፈት የሚወክለው በአፈፃፀም ችግር የሚከሰት ስህተትን ሲሆን በይሆናል ግምት እና በማዳጥ (Lapse) የሚፈጠር ስህተትም በዚህ ውስጥ የሚጠቃለል ነው፡፡ እንደ Brown (1994) ገለፃ ግድፈት በማንኛውም ሰው የሚፈፀም አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈትን የማይለይ ነው፡፡ አፍ ፈት ተናጋሪዎች ይህን ማዳጥ ወይም ግድፈት ወዲያውኑ ተገንዝበው ሊያስተካክሉት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ለአፍ ፈቶች የብቃት ማነስ ችግር ሳይሆን በአፍ ፈቶች ሂደት የተወሰነ ክፍተት ማመላከቻ ነው፡፡ ይህ ክፍተትም ምናልባት ጭንቀት፣ አፍ ማዳጥ ዘፈቀዳዊ የቋንቋ አጠቃቀም እና ወዘተ. ናቸው፡፡

ስህተት የምንለው ግን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት የተለየ ስርዓት ባለው መንገድ አፈንግጠው የሚጽፉትን ወይም የሚናገሩትን ሲሆን የተማሪዎቹን የቋንቋ ብቃት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-በአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ግሶች የሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታ ቦዝ ቅርጽ የመጨረሻ ድምጽ፣ ‹ኦ› ነው፡፡ ይህም ሰበራ ብሎ ሰብሮ፣ ሄደ ብሎ ሄደ፣ መነዘረ ብሎ መንዝሮ በማለት ይገልፃል፡፡ ይህን የተረዳ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ‹ፈነጨ› የሚለውን ግስ ወደ ቦዝ ለመለወጥ “ፈንጮ” ቢል ስህተት ሰራ እንለዋለን፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስህተት ይሁን ወይም ግድፈት ለመረዳት በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ‹ሰለቸ› እና ‹አገኘ› የሚሉትን ቃላት ወደ ቦዝ ለመለወጥ በቅደም ተከተል “ሰልቾ” እና “አግኞ” ብሎ ከተጠቀመ በትክክል ስህተት ነው ብለን መደምደም ያስችለናል በማለት Brown (1994:200) ያስረዳሉ::

## 2.1.2. የስህተት ምንጮች

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ፍንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ በጣም በርካታ የሆኑ ምክንያች እንዳሉ የሁለተኛ ቋንቋ መማርን አስመልክቶ ከተፃፉት ድርሳናት ውስጥ መመልከት ይቻላል፡፡ ቀደም ባሉት ክፍሎች ለመጠቆም እንደተሞከረው የስህተት ትንተና ዘዴ ከመጀመሩ በፊት የነበረው የንጽጽራዊ ትንተና ያተኩር የነበረው የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር በማነፃፀር የችግሩን ምንጭ ማሳየት ይቻላል በሚል ሀሳብ ላይ ነበር፡፡ ይህንን ሀሳብ Dulay (1982:144) ቋንቋ በመማር ወይም በመልመድ ሂደት የሚከተለውን የስህተቶች ምንጭ የውጫዊና ውስጣዊ ተጽእኖዎች ድምር ውጤት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህሩ የስልጠና ሂደቶች የተማሪዉ ባህላዊ አዉዶች፣ለቋንቋዉ የሚኖረዉ ተጋልጦ እና የመሳሰሉት ዉጫዊ እና እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር የሁለተኛ ቋንቋን ህግጋት በተግባቦት ሂደት ለመተግበር ሲሞክር የሚጠቀምባቸዉ የተሳሳቱ መላምቶች ከተማሪዉ ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ዉስጣዊ ጉዳዮች የተናጠልም ሆነ የጋራ ድምር ዉጤት ናቸዉ፡፡

የስህተት መንስኤን Ellis (1994:62-63) በስህተት ትንተና ሂደት የአንድን ስህተት ምንጭ በእርግጠኝነት መናገር በጣም አስቸጋሪ እና አሻሚ ለሆን ይችላል በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም Dulay (1982:144) የስህተት ምንጮች መላምታዊ ናቸዉ በማለት ያሰረዳሉ፡፡ ይህ ጥናት በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች

የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይቻላሉ ተብለው በበርካታ የመስኩ ባለሙያዎች ተዘዉተረው የሚጠቀሱ መላምቶችን ማለትም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣የውስጥ ቋንቋ ተጽእኖ፣የመማር ማስተማር ሂደት ድክመትና የስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በአጭሩ ይቀርባሉ።

### 2.1.2.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ከስህተት ምንጮች ውስጥ አንዱ ነው። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አዲስ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ የቀደመው ቋንቋ ጣልቃ የሚገባበት ሂደት ነው በማለት Jackson (1987:101), Norrish (1992:22), Dulay (1982:171) ያስረዳሉ። ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የተወሰነ ክፍተት ሲያጋጥማቸዉ ያን ክፍተት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉን ተጠቅመዉ ሊሞሉት ይሻሉ። ይህ ጣልቃ ገብነት ብዙን ጊዜ ሳይታሰብ የሚከሰት ሲሆን ጎልቶ የሚታየዉም ተመሳሳይነት ባላቸዉ ቋንቋዎች መሃል ነዉ። ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ የተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ተፅዕኖ ተማሪዉ ለሚፈፅማቸዉ ስህተቶች እንደ አንድ ምክንያት ሊቆጠር እንደሚችል በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፤ እንደ Dulay (1982:96) በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመማር ሂደት ጣልቃ እየገባ በሚያደርሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ የተነሳ ስህተት ሊፈፅም ይችላል። ከእነዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Norrish (1992:22) ሲገልፁ ቋንቋን የመማር ሂደት የልምድ ክምችት ዉጤት በመሆኑ የተማሪዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል።

የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዉ በድምፅ፣በቃላት አጠቃቀም፣በሐረጋትና በዐረፍተ ነገር አወቃቀር ዉስጥ ሊስተዋል የሚችል ቢሆንም ስህተቱ ጎልቶ የሚታየዉ ግን በንበት በመሆኑ ከንግግር ቅላፄ (ቃና) በመነሳት የተናጋሪዉን ማንነት ማወቅ እንደሚቻል Edge (1989:7-9) ያብራራሉ። በሌላ በኩል Negara (1983:36) እንደሚገልፁት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መሰረታዊ የስህተት ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ተፅዕኖ ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የታላሚዉን ቋንቋ ቅርፅ ከአፍ መፍቻ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ወይም ተቀራራቢነት ባለዉ መንገድ ያመነጫል።

ይህ ከአፍ መፍቻ ቋንቋዉ መዋቅር ጋር ተቀራረቢነት ያለዉ አጠቃቀም ከታላሚዉ ቋንቋ ትክክለኛ መዋቅር የፈነገጠ ሲሆን ተማሪዉን ለስህተት ይዳርጋል። ተማሪዉ ታላሚዉን ቋንቋ እየተማረዉ ሲሄድ አፍ መፍቻ ቋንቋዉ ከታላሚዉ ቋንቋ ጋር ይበልጥ እየተዋሃደ የሚሄድ በመሆኑ የሚፈጠሩ ስህተቶችም ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ይገመታል። በተጨማሪም Ellis (1989:24) እንዳስቀመጡት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የተነሳ

ከተፈጠሩት ስህተቶች በተጨማሪ በግምታዊ መልስ በቂ ልምምድ ባለማድረግ የታላሚውን ቋንቋ ህግ ህጉ በማይሰራባቸው ቦታዎች በመጠቀም የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶች እንዳሉ አመልክተዋል፡፡

### 2.1.2.2. የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ

ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ በተወሰነ ደረጃ ከመጋለጡ የተነሳ ያገኛቸውን ጥቂት ወይም የተወሰኑ የቋንቋውን ስርዓቶች በመጠቀም በንግግር ወይም በጽሁፍ ሀሳቡን ለመግለጽ ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ ስህተት ሊፈጽም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉ ስህተቶች ምንጫቸው የታላሚ ቋንቋዎች ውስብስብ ባህሪይ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ስህተቶች በመሆናቸው ስህተቹ በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት Norrish (1992), Littlewood (1984) ይገልፃሉ፡፡ በምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በውስጠ ቋንቋ ውስብስብ ባህሪይ ተጽዕኖ ስህተቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን የቋንቋውን ውስብስብ ስርዓቶች ለተግባቦታዊ ተግባር ለማዋል ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት ተማሪው ስህተት ሊፈጽም ይችላል፡፡

በተጨማሪም Richards (1974), Dulay(1982), Littlewood (1984) በዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች የታላሚዉን ወይም ለትምህርት የቀረበዉን ቋንቋ ስርዓት በማፋለስ የሚፈጠሩ ስህተቶች መሆናቸዉን ይገልፃሉ፡፡ በዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች ተማሪዉ በታላሚዉ ቋንቋ የሚያሳያቸዉን መሻሻሎችና እድገትን የሚጠቁሙ ፍንጮች በመሆናቸዉ እድገታዊ ስህተቶች ሊባሉ እንደሚችሉ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ በስህተት ትንተና ላይ የተሰማሩና ጥናታቸዉን ያካሄዱ ተመራማሪዎች በጥናታቸዉ እንዳረጋገጡት አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች ቀድሞ ከነበረዉ እምነት በተፃራሪ በእድገታዊ ስህተቶች ወይም ዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚከሰቱት ስህተቶች ናቸዉ ሲሉ Dulay(1982፡164) ይገልፃሉ፡፡

ተማሪዎች በዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች ምንጭ አንዱ የተሳሳተ ማጠቃለያ ላይ በመድረስ የሚፈፅሟቸዉ ናቸዉ፡፡ የተሳሳተ ማጠቃለያ ስንል ተማሪዎች ታላሚዉን ቋንቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አዲስ ስርዓት መሰረት አድርገዉ በቋንቋዉ ለመጠቀም ሲሞክሩ የሚሳሳቱትን ማለታችን ነዉ፡፡ ይህም ታላሚዉ ቋንቋ በአብዛኛዉ የሚጠቀምበት የራሱ መዋቅር ይኖረዉና ያመዋቅር በሁሉም የማይሰራ ከሆነ ተማሪዎች መዋቅሩን ባጠቃላይ ለቋንቋ እንደሚሰራ አድርገዉ ሲቀበሉትና ሲጠቀሙበት

የሚፈጠረዉን ስህተት ያሳያል። ለምሳሌ፦ በአማርኛ ቋንቋ በላ ብሎ ብላ እንደሚባል የተረዳ ተማሪ መጣ የሚለዉን ቃል ምጣ ቢል በተሳሳተ ማጠቃለያነት የተነሳ ነዉ ማለት እንችላለን (Norrish,1992:31-32, Littlewood፣1984:23)።

Dulay et. al.(1982:138-139) በበኩላቸዉ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳላቸዉ በመግለጽ እንደሚከተለዉ ዘርዝረዋቸዋል።

1. ድግግሞሽ(double marking):- በአንድ አረፍተ ነገር ዉስጥ አንድን የቋንቋ ቅርጽ አንድ ጊዜ ብቻ መጠቀም ሲገባ ያንኑ ቅርጽ በሌላ መልኩ መድገሙ የተለያዩ ስህተቶችን ሊያስከትል ይችላል።

2. የተሳሳተ ድምዳሜ(faulty over generalization):- ተማሪዉ ለትምህርት የቀረበዉን ቋንቋ ህግ ቀደም ሲል በለመደዉ ህግ አጠቃሎ ለመጠቀም ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት የሚከሰት ስህተት ነዉ። በዚህም የተነሳ በታላሚዉ ቋንቋ ተቀባይነት የሌላቸዉን ህግጋት ለመጠቀም ሙከራ ሲያደርግ ለተሳሳተ ማጠቃለያ ሊጋለጥ ይችላል።

3. እክላ(simple addition):- በቦታዉ አላስፈላጊ የሆነ ድምጽን ፣ ምዕላድን ወይም ደግሞ ቃልን በመጨመር ሊፈጠር የሚችል ስህተት ነዉ።

4. ግድፈት(omission):- በአንድ አረፈተ ነገር መዋቅር ዉስጥ መገኘት የሚገባዉ ተዋቃሪ ሳይገኝ በመቅረቱ ምክንያት ሊፈጠር የሚችል ስህተት ነዉ።

5. የቅደም ተከተል መፋለስ :- የቋንቋዉ ስርዓት በማይፈቅደዉ መልኩ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን አለቦታቸዉ በማስገባት የሚፈጠር ስህተት ነዉ።

የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ተማሪዉ የታላሚዉን ቋንቋ በከፊል ብቻ ተረድቶ ሀሳቡን በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ለመግለጽ ሲሞክር የታላምዉ ቋንቋ ዉስብስብነት ባህሪ ለስህተቶች የሚዳርግበት መንስኤ ሊሆን ይችላል።

### 2.1.2.3. የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች መካከል የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የማስተማያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ተጠቃሽ እንደሆኑ በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ። እነዚህን የስህተት ምንጮች Negra (1983:40) ውጫዊ

ተጽእኖዎች ሲኗቸው Brown (1994:215-217) ደግሞ የትምህርት አውድ ችግር ይኗቸዋል፡፡ ይኸዉም አውድ የሚለው ቃል የመማር ክፍልን ከመምህሩ እና ካሉት የትምህርት መሳሪያዎች ጋር አንድ ላይ የያዘ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም አውድ በትምህርት ሂደት ወቅት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠናከሪያነት ከማዋል ይልቅ በትምህርቱ ላይ ተጽእኖ ሲያሳድር ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል Norrish (1992:12) ደካማ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ተማሪዎች ስህተት እንዲፈፅሙ ምክንያት ስለሚሆን መምህሩ በቋንቋዉ ትምህርት ሂደት ሲፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ለመቅረፍ ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥና በመከተል በተማሪዎቹ ፍላጎቶች የቋንቋ ችሎታና ከመሳሰሉት ነጥቦች ጋር እያገናዘቡ የቋንቋ ይዘቶችን ማደራጀት እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም Broughton (1978:134) በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ስህተት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ከሚችሉ ነገሮች ዉስጥ መርሃ ትምህርቱ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ መምህራንና ተማሪዎች ይጠቀሳሉ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

የስህተት አስተራረም ዘዴን በተመለከተ መምህራን የተማሪዎችን ስህተት እንደ አንድ የማስተማሪያ ስልት መቀየሻ አድርገዉ ሊወስዱት ይገባል፡፡ይኸዉም ስህተቱ ከታረመ በኂላ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ ሲሰጥ ዘዴን የተላበሰና ሞራላቸዉን የማይነካ መሆን አለበት፡፡ምናልባት ስህተትን መስራት እንደማይጠበቅ ነገር ቆጥሮ አበረታች ያልሆነ ሃሳብ የሚሰነዝር ከሆነ፣ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ያላቸዉ ፍላጎት ሊቀንስ ይችላል፡፡የስህተት አስተራረምን በተመለከተ Raimes(1983:22) የሚከተሉትን አራት ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡

1. መምህር የተማሪዎቹን ስህተት በበጎ እንጂ በመጥፎ ጎኑ ፈርጆ መመልከት የለበትም፡፡ምክንያቱም ስህተት የተማሪዎቹን የእዉቀት ደረጃ አመላካች ከመሆኑም ባሻገር የትምህርቱ ሂደት ምን ላይ እንዳለ ተጨባጭ ማረጋገጫ በመሆን ያገለግላል፡፡

2. ለቀጣዩ ፅህፈት ትምህርት እቅድ ለማዉጣት የተማሪዎችን ስህተት መመልከት ጠቃሚ ነዉ፡፡በዚህም ተማሪዎች በቀጣይ ምን መስራት እንደሚገባቸዉና ምን ምን ነገሮች እንደሚያስቸግሯቸዉ ያሳያል፡፡

3. መምህሩ የተማሪዎቹን ስህተት ከማረሙ በፊት ተማሪዎቹ ራሳቸዉ ሊያርሙ የሚችሉበትን አጋጣሚ መፍጠር አለበት፡፡ራሳቸዉ ለማረም ከቻሉ ስህተት

የሰሩበትን ምክንያት ለይተዉ ለማወቅ ይችላሉ፡፡ምክንያቱን ማወቅ ደግሞ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለዉ፡፡

4. በተማሪዎቹ የጽሁፍ ስህተት እርማት ላይ የመምህሩ ትኩረት መሰረታዊ በሆኑት ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡መሰረታዊ የሚባሉትም የዐረፍተነገሩን ሀሳብ ሊያዛቡ የሚችሉት ናቸዉ፡፡

### 2.1.2.4. ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

Norrish (1992:19) እንደሚሉት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ ተማሪዎች ስህተቶቹን እንዲፈጽሙ የሚያደርጋቸው ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ነው፡፡ ስነልቦናዊ ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ ስህተቶችም በcorder “ያላስፈላጊ ድግግሞሽ” ተብለው መጠራታቸውን Norrish (1992) የገለጹ ሲሆን እነዚህ ስህተቶች ከቋንቋ መማር ጠቃሚ ክፍሎች ከሚቆጠሩት ስህተቶች የተለዩ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡

በተጨማሪም Richards (1974)፣ Richards and Sampson(1990) እና Norrish (1992) ተማሪዉ ለታላሚዉ ቋንቋ ያለዉ አመለካከት፣ቋንቋዉን ለመማር ያለዉ ፍላጎትና የመሳሰሉ ሁኔታዎች ቋንቋዉን በመማር ሂደት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ የስነ ልቦና ሁኔታዉ ቋንቋዉን በመናገር ወይም በመፃፍ ሂደት ላይ ስህተት እንዲፈፅም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸዉ አመለካከት ከቤተሰቦቻቸዉ ሊወርሱ እንደሚችሉ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም ወላጆች ለታላሚዉ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያላቸዉ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት በልጆቻቸዉ ላይ ሊንፀባረቅባቸዉ እንደሚችል እንረዳለን፡፡

ተማሪዉ ለሚማረዉ ቋንቋ የሚኖረዉ አዎንታዊ አመለካከት ቋንቋዉን በፍላጎት እንዲከታተለዉ ሊያደርግ ሲችል በተቃራኒ ተማሪዉ ለቋንቋዉ የሚኖረዉ አሉታዊ አመለካከት ደግሞ ተማሪዉ ቋንቋዉን እንዲጠላዉና የመማር ፍላጎቱን እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ ይህንን Ellis (1994) እና Groarty (1996) የተለያዩ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ለሚማሩት ቋንቋ ተነሳሽነትና አዎንታዊ አመለካከት የነበራቸዉ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ዉጤታማ መሆን ሲችሉ በሌላ በኩል ደግሞ ለታላሚዉ ቋንቋ አሉታዊ አመለካከት ያለዉ ተማሪ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ስለሚሆን ሃሳቡን በፅሁፍ ለመግለፅ በሚሞክርበት ጊዜ ስህተት እንዲፈፅም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

### 2.1.3. የስህተት ትንተና ዘዴዎች

የስህተት ትንተና ለማካሄድ እስከ አሁን ድረስ ወጥነት ያለው ዘዴ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በትንተናው ዙሪያ በጣም ብዙ የስህተት አይነቶች በመፈጠራቸው የተነሳ የስልቶቹን ዓይነት በመመደቡ ላይ ልዩነቶች እየሰፉ መጥተዋል፤ በዚህም የስህተት ትንተናን ትልቅ እንቅፋት አጋጥሞታል በማለት Lott (1983:256) ይገልፃሉ:: ይሁን እንጂ በብዙዎች ዘንድ በሰፊው የሚሰራባቸው የስህተት ትንተና ዘዴዎች እንዳሉ Dulay (1982፡146-197) ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህ መካከልም የስነ ልሳናዊ ክፍሎችን መሰረት ያደረገ፣ የዐረፍተ ነገር ላዕላይ መዋቅርን መሰረት ያደረገ፣ ንጽጽራዊ ክፍልን መሰረት ያደረገ፣ተግባቦትን መሰረት ያደረገ ሲሆን እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባል፡፡

#### 2.1.3.1. የስነ ልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በርካታ የስህተት ትንተና ዘዴዎች በስነ ልሳናዊ የመዋቅር ክፍሎች ላይ ተመስርተው የተጠኑ ናቸው፡፡ ጥናታቸውም በአንዱ ስነ ልሳናዊ ክፍል ወይም በተወሰኑት አሊያም በሁሉም ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ የስህተት ትንተናው በስነ ድምጽ፣ በስነ መዋቅር፣ በቃላት፣ በስነ አገባብ፣ ፍች እና የዲስኩር ጠቋሚዎች ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ በዚህ ዘዴ ስህተቶችን ለመተንተን የሚፈልግ አጥኚ ስህተቶችን ከለቀመና ካሰባሰበ በኋላ እንደ ስህተቱ ዓይነት በተለያየ ስነ ልሳናዊ ምድብ ውስጥ እያስቀመጠ ይተነትናል፡፡ በርካታ አጥኚዎችም ስህተቶችን በስነ ልሳናዊ መዋቅሮች በመከፋፈልና በመተንተን ውጤታቸውን ይፋ ለማድረግ ተጠቅመውበታል፡፡ አንዳንድ አጥኚዎች ይህን ዘዴ እንደ ብቸኛ የስህተት መተንተኛ ስልት ይቆጥሩታል፡፡ በዚህ ዘዴ አጥኚው አስቀድሞ ለማጥናት ካቀዳቸው የስህተት አይነቶች ውጭ ለሆኑ ስህተቶች ትኩረት አይሰጥም በማለት Dulay (1982:146-150) ያብራረሉ፡፡

#### 2.1.3.2.የዐረፍተ ነገር ቅርጾችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የሚጽፏቸው ዐረፍተ ነገሮች ውጫዊ ቅርጽ ስንመለከት የተለያዩ ዓይነት ስህተቶች ያሉባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ ዐረፍተ ነገር አካልን ሊገድፉ ወይም የማያስፈልጉትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋውን ቅርጽ አላግባብ ሊያሰፍሩ፣ አንዱን የዐረፍተ ነገር አካል ከሌላው በማስቀደም ቅደም ተከተል ሊያዛቡ፣ ለአንድ አገልግሎት ለምሳሌ ለእምርነት ሁለት ምልክቶች ሊጠቀሙ እንሚችሉ Dulay (1982) ያብራረሉ፡፡

በመሆኑም ይህ ዓይነቱ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በዐረፍተ ነገር ውጫዊ መዋቅር ላይ የሚታይ ስህተቶችን ይመለከታል፡፡ ይህ ዘዴ አንድን አዲስ ቋንቋ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ

ለመማር ተማሪው በምን አይነት አእምሮአዊ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍና ቋንቋው ምን አይነት መንገድ ተጠቅሞ እየለመደው እንዳለ የሚጠቁም መረጃ ለመስጠት ከማገልገሉም በላይ ተማሪው በሚማረው ቋንቋ ላይ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ይብዛም ይነስም የተወሰነ ተጠያቃዊ አካሄድ ላይ የሚመሰረት እንደሆነ እንድንገነዘብ ያስችለናል (Dulay,1982)፡፡

በዐረፍተ ነገር ላዕላይ ቅርጽ ላይ የሚመሰረት የስህተት ትንተና ዘዴ መነሻው ተማሪዎች በሚጽፏቸው ዐ.ነገሮች ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ናቸው፡፡ ይህንን ዘዴ በስነ ልሳናዊ መዋቅር ላይ ተመስርቶ ከሚተነተነው የስህተት አከፋፈል ዘዴ የሚለየው አጥኚው ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶ ከማየቱ በፊት ስህተቶችን ለመመደብ የሚያስችለው የስህተት አከፋፈልና አተናተን ዘዴ አጥኚው ስህተቶችን የሚመድበው ተማሪዎቹ የፈጸሟቸውን ስህተቶች መሰረት በማድረግ ነው በማለት Dulay (1982:150-162) ይገልፃሉ::

### 2.1.3.3.ንጽጽራዊ ክፍፍል

ንጽጽራዊ ትንተና መሰረት የሚያደርገው የስህተት ትንተና ዘዴ የሚያተኩረው በታላሚው ቋንቋ አፈ ፊትና በታላሚው ቋንቋ ኢ-አፈ ፊት የሆኑ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ እና መማር ሂደት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በማነፃፀር ላይ ነው፡፡ ይህንንም Dulay (1982) በምሳሌ ሲያብራራ አፉን በኮሪያ ቋንቋ የፈታ ሰው እንግሊዘኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማር የሚፈጽመው ስህተትና እንግሊዘኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ሲማር የሚፈጽመው ስህተትና እንግሊዘኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት እየለመደ ያለ ህፃን ልጅ የሚፈጽማቸውን ስህተቶች በማነፃፀር ለመተንተን ሙከራ ሲደረግ በንጽጽራዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ የስህተት አከፋፈል ዘዴ መተግበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ አማካኝነትም በታላሚው ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ህፃናት የሚፈጽማቸው ስህተቶች ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ የሚፈጽማቸውን ስህተቶች በመተንተን ኢ-አፈ ፈቱ ተማሪ ያጋጠመው ችግር የአፍ መፍቻ ቋንቋው ጣልቃ ገብነት አልያም ደግሞ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውጤት መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል በማለት Dulay (1982፡163-172) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.3.4.ተግባቦታዊ ተጽእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል

በዚህ ዘዴ ስህተቶች የሚከፋፈሉት ተግባቦትን ከማወካቸው አንፃር ነው፡፡ በንጽጽራዊ ትንተና እና በዐረፍተ ነገር ላዕላይ መዋቅር ላይ የተመሰረቱ የስህተት ክፍፍሎች በራሳቸው

በስህተቶቹ ገጽታ ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ተግባቦትን መሰረት በማድረግ የሚከፋፈሉት ስህተቶች ግን የሚያተኩሩት ከተግባቦት አኳያ አንባቢው ወይም አድማጩ መልዕክቱን በትክክል ከመረዳት ወይም ካለመረዳት አንፃር ነው፡፡ ይኸውም ተማሪው የሚናገራቸውን ሀሳቦች አድማጩ የማይረዳቸው ከሆነና ግልጽነት ከጎደላቸው የተግባቦቱ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የሚያተኩረው ተግባቦትን የሚያደናቅፉትንና የማያደናቅፉትን ስህተቶች ለይቶ በመተንተን ላይ ነው፡፡ በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የትኞቹ ስህተቶች ናቸው? አድማጩ መልዕክቱን እንዳይረዳ እንቅፋት የሆኑበት? የሚለው ጥያቄ አብይና መሰረታዊ ጥያቄ ነው፡፡

በመሆኑም Norrish (1992:80) እንደሚገልጹት የስህተት ትንተና ለማድረግ ሁለት አብይት ዘዴዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያውና በጣም የተለመደው ተማሪዎች ይሰሯቸዋል ተብሎ የሚገመቱትን የስህተት አይነቶች አስቀድሞ በመመደብ ስህተቶችን በየምደባቸው የማሰራጨት ዘደ ሲሆን ሁለተኛው ተማሪዎች የሰሯቸውን ስህተቶች መሰረት አድርጎ የስህተት አይነቶችን መበየን ነው፡፡ በመጀመሪያ ዘዴ የስህተት አይነቶች አስቀድመው የተመደቡ በመሆናቸው ተማሪዎቹ የሰሯቸውን ስህተቶች በየምድቡ በመከተት ለመተንተን ስለሚሞከር ለአሰራር ቀላል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዘዴ ስህተቶቹ በሚያሳዩት በራሳቸው ባህሪይ ለመከፋፈል አለመቻሉ ደካማ ጎን ነው፡፡ በሁለተኛው ዘዴ የስህተት ዓይነቶቹ በስህተቶቹ መሰረትነት የሚመሰረቱ ስለሆነ ከመጀመሪያው ዘዴ የተሻለ ነው፤ ሆኖም ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ለአሰራር አስቸጋሪ ነው በማለት Norrish (1992፡81-92) ያስረዳሉ፡፡ ከፍ ሲል የቀረቡትን አራቱን የስህተት አተናተን ዘዴዎችን በውስጡ ባጠቃለለ መልኩ Norrish (1992፡81-91) የስህተት አከፋፈልን በሁለት አብይት ክፍሎች ከፍለው እናገኛቸዋለን ይኸውም ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴና የተፈጸሙ ስህተቶን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴዎች ናቸው፡፡

*ሀ. ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ*

ይህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ተማሪው በአብዛኛው ሊፈጽማቸው ይችላል ተብለው በሚታሰቡት ስህተቶች ላይ በመመስረት የስህተት ትንተናው የሚካሄድበት ስልት ነው፡፡ በዘዴው የስህተቶቹ አይነት አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ በተማሪው ድርሰት ውስጥ የታዩት ስህተቶች በተወሰነላቸው ምድብ ውስጥ ይካተታሉ ፡፡

ለ. ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ

የዚህ ዘዴ ዋነኛ መሰረቶች በተማሪዎቹ የሚፈጸሙ የተለያዩ ስህተቶች ናቸው። ይህ ዘዴ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ካደረጉ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በተነፃፃሪ ስህተቶቹ እራሳቸውን የስህተት ምድባቸወን እንዲወስኑ የሚያደርግበት አሰራር ነው። ዘዴው Hudson (1971) በተባለ ምሁር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተተገበረ የሚነገር ሲሆን ስህተቶችን በአይነታቸው ለመለየት ካርድን እንደ ጥሩ መሳሪያ ይጠቀምበታል። በመጀመሪያ እያንዳንዱ ስህተት በካርዱ ላይ ይመዘገባል። በማስከተልም ከርዶቹ እንዲያዙት የስህተት አይነት በእየክፍሎቻቸው ይመደባሉ። ክፍሎቹ ባላቸው ተመሳሳይነት አንዱ በሌላው ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። እንደዚህ እየተደረገ በተቻለ መጠን ስህተቶቹን በአነስተኛ ምድብ ውስጥ ለማጠቃለል ይሞከራል። ከዚያም እንደሚያሳዩት ባህሪይ ትንታኔው ይካሄዳል። ይህ አቀራረብ ይበልጥ ለጽሁፍ ቋንቋ ተስማሚ ነው በማለት Norrish (1992፡83-86) ያስረዳሉ።

## 2.1.4. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ

ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መሳካትም ሆነ አለመሳካት የስህተት ትንተና የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። እንዲሁም በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ስነ ትምህርታዊ ፋዳዎች እንዳሉት ምሁራን ይገልፃሉ። የስህተት ትንተና ማካሄድ ታላሚውን ቋንቋ በመማር ማስተማሩ ሂደት እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ይህንን ሀሳብ Lott (1983:256) የስህተት ትንተና ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተቶች እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ቴክኒኮችን በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ ያለው ስራ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በተጨማሪም ተማሪዎቹ በታላሚዉ ቋንቋ ያላቸዉ ዕዉቀት ምን ያህል እንደሆነና ጠንክረዉ ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያስወግዱ እንዲሁም በየትኛዉ የታላሚዉ ቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተዉ መለማመድ እንዳለባቸዉ ሊጠቁም ይችላል። በአንድ ክፍል ዉስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች ቢኖሩ የጋራ ስህተታቸዉ የትኛዉ እንደሆነ በአንዱ ቋንቋ አፉን የፈታ ተማሪ ከሌሎች የተለየ የሚፈፅመዉ ስህተት ካለ የትኛዉን አይነት ስህተት እንደሚፈፅም እና የስህተቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል።

በዚህም Norish (1992:80) በበኩላቸዉ ከስህተት ትንተና ዉጠት ግንባር ቀደም ተጠቃሚ የቋንቋ መምህራን እንደሆኑ ሲገልጹ፣መምህራን ለሚያጋጥሟቸዉ አዳድስ ተማሪዎች ዳራዊ ዕዉቀት ይሰጣል􏰀ካገኙትም መረጃ በመነሳት የትኛዉን ይዘት በምን ዓይነት መልክና ለምን

ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸዉ እንድወስኑ ያግዛል። የተማሪዎችን ችግር በምፈታ መልኩ የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖር ያደርጋል። መለስ ቢለዉም የማስተማሪያ ስነ ዘዴዉ ያለበትን ደረጃ እንዲገመግሙ ይረዳቸዋል። ይኸዉም የተማሪዎቹ ችሎታ እየጨመረና ስህተታቸዉ እየቀነሰ ከመጣ የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴ አበረታች፤ የተማሪዎቹ ችሎታ መሻሻል ካላሳየ ወይም ባሉበት ደረጃ ከቆሙ ወይም ካሽቆለቆሉ ደግሞ የማስተማሪያ ዘዴዉ ችግር እንዳለበት ሊጠቁማቸዉ ይችላል።

በተጨማሪ የስህተት ትንተና ፣አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ ከሚፈጽማቸዉ ስህተቶች በመነሳት ተማሪዉ ስለታላሚዉ ቋንቋ ያለዉን ችሎታ ለመገምገም ስለሚያስችል፣ ስለተማሪዉ የተሻለ መረጃ በመስጠት ያገለግላል። ይህም ተማሪዉ የትኞቹን ቋንቋ ይዘቶች በይበልጥ መማር እንዳለበት ይጠቁማል። እንዲሁም የሚፈጽማቸዉንም ስህተቶች ከስነ- ልሳናዊ ክፍሎች አኳያ ከፋፍሎ በማስቀመጥ በቋንቋ መማር ሂደት ዉስጥ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች ለመለየት ይጠቅማል (Samuel 1987:102)። በአጠቃላይ ለመምህራን የተማሪዎቹን ችግር በመጠቆም የትኩረት አቅጣጫን በማሳየት የማስተማሪያ መሳሪያዉንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንድፈትሹ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል።

የስህተት ትንተና ለመምህራን ከሚኖረዉ ፋይዳ በተጨማሪ ለቋንቋ ተማሪዎች እና ለመርሀ ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Richards(1974:25)፣ corder (1973:257)፣ Norrish (1983:86) olsen (1991፡191)እናlengo(1995:20-21)እንደሚከተለዉ ይገልጻሉ።

ለተማሪዉ ከስህተቱ እንዲማር እንደመሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ይኸዉም የታላሚዉን ቋንቋ ህጎች ለመገልገል የሚጠቀሚባቸዉን ግምቶችና መላምቶች የስህተት ትንተና ለመምህራን ከሚኖረዉ ፋይዳ በተጨማሪ ለቋንቋ ተማሪዎች እና ለመርሀ ትምህርት አዘጋጆች ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ Richards(1974:25)፣ corder (1973:257)፣ Norrish (1983:86) olsen (1991፡191)እናlengo(1995:20-21)እንደሚከተለዉ ይገልጻሉ።

ለተማሪዉ ከስህተቱ እንዲማር በተግባር ለማረጋገጥና ለመፈተሽ ያስችለዋል።

ለቋንቋ ተመራማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዴት መማር እንደሚቻልና ተማሪዉ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት የሚጠቀምባቸዉን ብለሃቶችና ቅደም ተከተሎች በተመለከተ መረጃ በመስጠት ያገለግላል።

ለመርሃ-ትምህርት ቀራጮችና ለማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት በመርሀ ትምህርቱና በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ዉስጥ የትኞቹ ይዘቶች ቅድሚያ መስጠትና መደራጀት እንዳለባቸዉ ግንዛቤ ያስጨብጣል።

ሌላዉ መሰረታዊ ጉዳይ ምንም እንኳን የስህተትን መንስኤ ወይም ምንጭን መርምሮ ማግኘት ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ቢባልም፣አንድን ስህተት ወጥነት ባለዉ ሁኔታ ምንጩ ይኸ ነዉ ብሎ መደምደሙ አስቸጋሪ ነዉ (ellis 1994:62-63)::

## 2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸዉን ስህተቶች በመለየት ለስህተቶቹ መፈጸም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን ጠቁሞ ለማብራራት ቅይጥ የአጠናን ዘዴ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን ለዚህም ዘዴ ወሳኝ በመሆን ካገለገሉት መሰረታዊ ነጥቦች ልዩ ልዩ መጻህፍት፣የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች እና ልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ የቀረቡ ናቸዉ፡፡

ከእነዚህ መካከልም መሰረት (2003) በኦሮሚኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በማጥናት በውጤቱም የስህተት ዓይነቶች፡- የቋንቋ አጠቃቀም፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሀሳብ ስህተቶች እና ለመለየት ያልተቻሉ የስህተት አይነቶች መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡ ለስህተቶቹ መከሰትም ምክንያት ያደረጉት በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ በመማር ማስተማር ሂደትናበስነ ልሳናዊ ሁኔታዎች መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኦሮሚኛ ቋንቋ አምስት አናባቢዎች አሉት፡፡በአማርኛ ቋንቋ የድምጽ ስርዓት ዉስጥ የሚገኙ /ኧ/ እና /እ/ በኦሮሚኛ ቋንቋ ዉስጥ ባለመኖራቸዉ ተማሪዎቹ ‹‹እ›› ሳድስ አናባቢን ከሳልሱ አናባቢ ‹‹ኢ››ጋር ያተካኩታል፡፡በማለት ገልጿል፡፡ በዚህ በድርሰት ማፃፍና ጽሁፍ መጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የድርሰት መልመጃዎች በመተንተን ተጠቅሟል፡፡

ይህ ጥናት በተማሪዎቹ ጽሁፎች ላይ የሚታዩ የስህተት አይነቶችንና ምንጮች ለመለየት ቅይጥ የምርምር ሂደትን ይከተላል፡፡ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱም የጽሁፉን ሂደት ምልከታ

በማድረግ ድርሰት ማጻፍ ይሆናል። ይህን ጥናትና የመሰረት (2003) ጥናትን አንድ የሚያደርጋቸው ሁለቱም በኢ-አፈ ፈቶች ስህተት ትንተና ላይ መመስረታቸዉ ነዉ።

ግርማ ኃይሉ (2000) በጌድኦኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ሲሆን ፣በተማሪዎቹ ድርሰቶች ዉስጥ የተመለከታቸዉ ስህተቶችም፡- የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት ናቸዉ።ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጌድኦኛ ቋንቋ የድምጽ ስረዓት ዉስጥ የሚገኙ አናባቢዎች (ኢ፣ኤ፣ኣ፣ኡ እና ኦ )ሲሆኑ በአማርኛ ከሚገኙ ሰባት አናባቢዎች መካከል ሁለቱ (ኧናእ) የሉም በማለት አስረድቷል። በዉጠቱም ለማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ተገቢዉን ትኩረት መስጠት፣መምህራንን ከዘመናዊ የማስተማር ዘዴዎች ጋር ማስተዋወቅ፣አጋዥ መጽሀፍትን ማዘጋጀት፣በመማሪያ ክፍል ዉስጥ የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎችን ዳራ ከግንዛቤ ያላስገባ መሆን፣ተከታታይነት ያለዉን እርማት መስጠት ችግሮቹን ለማቃለል እነደ መፍትሄ ሀሳብ ሰንዝሯል።

የአምላክሰራ (2008) የአማርኛ አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት በቅይጥ የምርምር ዘዴ ተማሪዎቹን በቀላል የዕጣ ናሙና በመለየት መረጃዎችን ድርሰት በማፃፍ፣ የጽሁፍና የቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስባለች። በዚህም ሂደት የስህተት ምንጮቹ፡- የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት፣ የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት፣ የስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ መሆናቸውን በማስቀመጥ እንደ መፍትሔም የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ዘዴዎች አዘገጃጀት ማሻሻል፣ ተማሪዎች በፍላጎት እንዲማሩ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚሉ መፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

የአምላክሰራ ጥናትን ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚለዩት የእሷ በአማርኛ አፍ ፈቶች ላይ መሆኑ፣ መረጃ ለመሰብሰብ ከድርሰት ጽሁፍ በተጨማሪም ለተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን ቃለመጠይቅ መጠቀሟ ይጠቀሳሉ። የእኔ ደግሞ በኢ-አፍፈቶች ላይ የተመሰረተና የመረጃ አሰባሰቡም ድርሰት በማፃፍ ሂደቱን በምልከታ መከታተል እና ለመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ በመጠቀምሆኗል። ሁለቱንም ጥናቶች አንድ የሚያደርጋቸው በስህተት ትንተና ላይ መመስረታቸው እና ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴ መጠቀማቸዉ ነዉ።

ተመስገን (2001) "የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ (በሀዲያ ዞን በሽኤ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተካሄደ ጥናት) የተመስገን ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት አፃፃፍ ብልሃት ተዛምዶ ሲሆን የጥናቱ ግኝትም በመምህሩ  የማስተማር ዘዴና በተማሪዎቹ ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ተዛምዶ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የጠቀሳቸው በጽህፈት ክሂል መማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ትኩረት እሱ በሚፈልገው የድርሰት አፃፃፍ ህጎች ላይ መሆኑ፣ ተማሪዎችም ህጎቹን ስለሚከተሉ የመጻፍ ፍላጎታቸው ባለመጠበቁ መሆኑን አጥንቷል፡፡ እንደ መፍትሔም መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ብልሃት  ሊጠብቁ የሚችሉ ማስተማሪያ ዘዴዎች ቢጠቀሙ ተማሪዎቹ የድርሰት አፃፃፍ ህግ እንዲከተሉ ከማድረግ በራሳቸው ምርጫ እንዲጽፉ ቢደረግ የሚሉትና ሌሎችን አስቀምጧል፡፡

የተመስገን ጥናት በጽህፈት ክሂል ላይ በመመስረት የድርሰት አፃፃፍ ብልሃት ከማንሳቱ ውጭ ከአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ጋር ስለማያስተሳስር ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ይለያል፡፡ ነገር ግን የመሰረት (2003) እና የአምላክስራ (2008) በተለያዩ ሀገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ጽህፈት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች /Error /Analysis/ ላይ በማተኮራቸው ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ይህ ጥናት በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዙሪያ ጽህፈትን በተመለከተ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ባለመገኘታቸዉ ተማሪዎቹ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ መልዕክት ሲያስተላልፉ ከተለያዩ ስህተቶች ነፃ ያለመሆናቸዉና የስህተቶቹ ቅርፅም በአብዛኛዉ ተቀራራቢ መሆኑ ለምን ይሆን? የሚለዉን ለመፈተሽ ይሞክራል፡፡ ጥናቱ በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በደቡብ ክልል በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፈትሿል፡፡

ተገኘ (2000) አፋቸዉን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች ትንተና በሚለዉ ስር የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣የቋንቋ አወቃቀር፣የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ናቸዉ፡፡የስህተት ምንጮቹም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣የዉስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት እንዲሁም ስነልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ አስቀምጧል፡፡ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ የጠቀሰዉም በከፍኛ ቋንቋ ዉስጥ (ኸ) እና (እ) አናባቢዎች ባለመኖራቸዉ በእነዚህ

አናባቢዎች ምትክ የተለያዩ ድምጾች በመተካት ስህተት ይፈጽማሉ፤በማለት ለአብነትም (ኧ) በሚገባበት ቦታ (ኤ)ን ሲጠቀሙ እንደተስተዋለ ገልጿል።

ይህ ጥናት በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና ሲሆን ተማሪዎች የፈጸሟቸዉ ስህተቶችም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣የቋንቋ አወቃቀር ስህተት እና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ናቸዉ።የስህተት ምንጮቹም የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ክፍተት ናቸዉ።የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖን እንደ አንዱ ምንጭ ለማስቀመጥም የAmbassadder Neecreraasha Apari Bacuri (2000) Dictionary ላይ መነሻ በማድረግ የሸክኛ ቋንቋ ሃያ ሰባት ድምጾች መካከል አምስቱ ቋሚ አናባቢዎች የሚባሉት 1.aአ 2.eኤ 3. Iኢ 4.oኦ 5.uኡ ናቸዉ። ሸክኛ ቋንቋ (ኧ) ና (እ) አናባቢዎች የሉም።በእነዚህ ምትክም (ኤ) ና (ኢ) አናባቢዎችን በመተካት በዉል ሳይለዩ እንደሚጠቀሙ ከስህተቶቻቸዉ ተስተዉሏል።በተጨማሪም በሸክኛ ቋንቋ ግንደ ቃል ወይም ስርወ ቃል መመስረት የማይችሉ ስድስት ተነባቢያን l,j,p,s,r,ch, ፣አስራ ስድስት ተናባቢያንና አምስት አናባቢያን የሚጠሩ ቃላት አጨራረሳቸዉ በአብዛኛዉ በ (oኦ) ድምጽ መሆኑን ስለ ቋንቋዉ ስርዓት ከተጠቀሰዉ ምንጭ መረዳት ይቻላል።

# ምዕራፍ ሦስት፤የአጠናን ዘዴ እና ንድፍ

## 3.1 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ቅይጥ የአጠናን ዘዴን በተግባር ላይ ማዋል ተመራጭነት ያለዉ ሆኖ አግኝቷል። ቅይጥ አጠናን ዘዴ አንድ የምርምር ስራ መጠናዊ እና ዓይነታዊ የምርምር አቀራረቦችን በጣምራ መጠቀም እንደሆነ (Almalk 2016÷291) ይገልፃሉ። በዚህ መሰረት ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ዉስጥ የተስተዋሉ የስህተት ዓይነቶች ምን ይመስላሉ? የስህተት ምንጮቹስ? ለሚለዉ ዓይነታዊ ምርምርን በመጠቀም የስህተት ብዛቱ ምን ያህል ነዉ? ለሚለዉ ደግሞ መጠናዊ ምርምርን ተጠቅሟል

## 3.2. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነዉ ገላጭ ጥናት ተመራማሪዉ የሚያጠናዉን ባህሪ ትረካዊ በሆነ መንገድ በአንባቢዉ አእምሮ ዉስጥ ስለ ጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ባልተሞካሸ፣ባልተንኳሰሰና እዉነታዉን በማያደበዝዝ መልክ ለማቅረብ የሚያስችል ንድፍ ነዉ። (ያለዉ 2006 38-40)

ይህ ጥናት በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮችን ተንትኗል

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በደቡብ ክልል በሸካ ዞን የኪ ወረዳ ከሚገኙ አራትየመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአንድ ትምህርት ቤት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም ትምህርት ቤት ኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የትምህርት ቤቱ አመራረጥም በአመቺ ናሙና /Convenience Sampling/ ስልት ነው። አመቺ ናሙና ስልት የተመረጠበት ምክንያትም ከቦታ ርቀት አንጻር ለአጥኚዋ የስራ አካባቢ ቅርብ ቢሆን ጥናቱን በቅርበት ለመከታተልና በጥናቱ የሚሳታፉ መምህራንና ተማሪዎችን መረጃ የመስጠት ትብብር በቀላሉ ለማግኘት ስለሚያስችል ነዉ

### 3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በትምህርት ቤቱ በየምድብ ክፍሎቹ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር እስከ 40 የሚደርስ ሲሆን አጠቃላይ ብዛታቸው 80 ነው፡፡ በጥናቱ የሚሳተፉትን ተማሪዎች ለመምረጥ ከየምድብ ክፍሎቹ ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ረድፋዊ ናሙና ዘዴን (Systmatic sampling method) በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ይህ የንሞና ዘዴ ተመራማሪዉ የጥናቱን አካባይ ጠቅላላ ብዛት ለናሙናነት ሊወስዳቸዉ በሚፈሊጋቸዉ አባላት ብዛት በማካፈል፣በተገኘዉ ዉጤት አንፃር ከጥናቱ አካባይ የስም ዝርዝር በተወሰነ የረድፍ ርቀት ላይ የሚገኙትን ሰዎች ወይም ነገሮች መዉሰድ ነዉ፡፡(ያለዉ 2006፣123-124) በዚህ ሂደት አጠቃላይ 80 ተማሪዎችን ለናሙናነት ለሚወሰዱት 40 ተማሪዎች በማካፈል የተገኘዉ ዉጤት ሁለት ሲሆን ቀድሞ ከተዘጋጀዉ የተማሪ ስም ዝርዝር ሁለት ፣ሁለት ተማሪዎች እየተዘለሉ ከየምድብ ክፍሎቹ 40 ተማሪዎች በረድፋዊ ናሙና ዘዴ (Systmatic sampling method) ድርሰት ጽፈዋል፡፡

### 3.3.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የክፍል ደረጃውን ለመወሰን ታላሚ የናሙና ስልትን በመጠቀም 9ኛ ክፍል ተመርጧል፡፡ ይህ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ችግሩ በሰፊዉ የታየበትና ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ የተሸጋገሩበት የክፍል ደረጃ እርከን በመሆኑ ነዉ 

### 3.3.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ 9ኛ ክፍልን በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን ሁለት በመሆናቸዉ በጠቅላይ የንሞና ዘዴ (comprehensive sampling) በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የተመረጡት ድርሰቶች እና መጠይቆች ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሆነው ድርሰት በተጠኚ ተማሪዎች የተፃፈ ሲሆን የጥናቱ ዓላማ የሆኑትን በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የታዩ የስህተት ዓይነቶች ተለይተዉ የስህተት ምንጮችን መመርመር የሚያስችሉ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

### 3.4.1. ድርሰቶች

የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ድርሰት ማጻፍ ነው፡፡ ድርሰቱ እንዲፃፍ ከመቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ እድሜና ዳራዊ የእውቀት ደረጃቸውን ባገናዘበ

መልኩ ስድስት ርዕሶች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዉ የቀርቡ ሲሆን ሁለቱ ርዕሶች ደግሞ ተማሪዎች በፍላጎታቸዉ መርጠዉ የፃፏቸዉ ናቸዉ፡፡እነዚህም በትምህርት መስኩ ባለሙያዎች ግምገማና አስተያየት ከተሰጠባቸዉ በኋላ አሁን ከሚታዩት ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የሚገናኙ እና ለሁሉም ተማሪዎች ስሜት ሊቀርቡ የሚችሉ ርዕሶች እንድሆኑ ተደርጓል፡፡ ድርሰቶቹንም በማፃፍ ሂደት በተዘጋጀው ርዕስ ዙሪያም ሆነ በመረጡት ርዕስ ላይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ 40 ተማሪዎች 64 ድርሰቶችን ፅፈዋል፡፡ የድርሰቶቹ የአስተራረም ሂደት መሰረት ያደርገዉ የNorrish (1992፣81- 91) ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ሲሆን እነዚህም፡- በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ስር (የሆሄያት ቅርጽ፣የቃላት አመራረጥ፣የቃላትድግግሞሽናየቃላት፣ጭመራ) በቋንቋ አወቃቀር ወይም ሰዋሰዉ ስህተት ስር (የጾታ፣የመደብ፣የቁጥር፣የመስተዋድድና የተሳቢ) በሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ስር (የነጠላ ሠረዝ፣የአራት ነጥብ፣የድርብ ሠረዝ )ስህተቶች ታርመዋል፡፡

### 3.4.1.1 የድርሰት መልመጃዎች አተናተን

ሁለት አበይት የስህተት መክፈያ ዘዴዎች እንዳሉ ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ እነርሱም፡- ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴና ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ናቸው በማለት Norrish (1992:81- 91) ይገልፃሉ:: ከነዚህም ውስጥ አጥኚዋ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴን ተጠቀማለች፡፡ በዚህም መሰረት የድርሰት መልመጃዎቹ አተናተን

1. በየገጹ ቃላቱን መቁጠርና ሁሉም ድርሰቶች የተፃፉባቸውን ቃላት በመደመር ጠቅላላ ድርሰቶች የተፃፉባቸውን ቃላት ብዛት ማወቅ፣
2. የተገኙትን የቃላት ብዛት ተጠኚ ተማሪዎቹ ለፃፏቸው ድርሰቶች ቁጥር ማካፈልና እያንዳንዱ ድርሰት የተፃፈበትን አማካይ የቃላት መጠን ማግኘት፣
3. በድርሰቱ ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶችን መቁጠርና አጠቃላይ ስህተቶችን ብዛት ማወቅ፣
4. በአጠቃላይ የተገኙ ስህተቶችን በአጠቃላይ በተፃፈው የድርሰት ብዛት በማካፈል አማካይ ስህተቱን ማግኘት፣

5. የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና በተገኘው ውጤት ድርሰቶቹ በተፃፉባቸው ቃላት መጠን በማካፈል በመቶ ቃላት ውስጥ ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ማወቅ፤

6. በመጨረሻም የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ነገሮች ለመገመት የተከሰቱ ስህተቶችን በመመርመር አጥኚዋ ከላይ የቀረበውን Norrish (1992:103-104) ስህተት አተናተን ስልት ተጠቅማለች፡፡

### 3.4.2 መጠይቆች

መጠይቆች አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ እንደመሆናቸዉ መጠን በድርሰቶች አማካይነት ሊፈተሹ ያልተቻሉ የስህተት ምንጮችን ሊያስገኙ ስለሚችሉ በተማሪዎች የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች እና በመምህራን የተመለሱ ቃለ መጠይቆች ናቸዉ፡፡

#### 3.4.2.1 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

በተማሪዎች የሚሞላዉ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡እነርሱም ክፍል አንድ የተማሪዉን አጠቃላይ መረጃ የሚሹ፣ክፍል ሁለት የሊከርት ስኬልን መሰረት አድርገዉ የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸዉ፡፡የጽሁፍ መጠይቆቹም በ27 ወንዶችና በ13 ሴቶች በድምሩ በ40 ተማሪዎች ተሞልተዋል፡፡

#### 3.4.2.2 የመምህራን ቃለ መጠይቅ

ከመምህራን የሚገኘዉ ምላሽ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ ተብለዉ የሚታሰቡ መረጃዎችን ሊያስገኙ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ቃለ መጠይቆቹም በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃ አማርኛን በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተመልሰዋል፡፡

### 3.5. የመረጃ  አተናተን

ጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የተጠቀመዉ በተማሪዎች የተፃፉ ድርሰቶችን፣በተማሪዎች የተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆችንና ከመምህራን የተገኙ ቃለ መጠይቆችን ሲሆን በዚህ ሂደት በተማሪዎች ፅሁፍ ዉስጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች በገላጭ ስልት ተብራርተዋል፡፡ ከየምድብ ክፍሎቹ በረድፋዊ ናሙና ዘዴ 40 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ተማሪዎቹም በአማራጭነት የቀረበላቸዉን ስድስት ርዕሶችና

ከራሳቸዉ የመረጧቸዉን ሁለት ርዕሶችን መሰረት በማድረግ በሁለት ዙር 64 ድርሰቶችን ፅፈዋል፡፡ የድርሰት መልመጃዎቹ አተናተንም ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ የተፈፀሙ ስህተቶች በዓይነት ዓይነታቸዉ ተለይተዋል፡፡በዚህም መሰረት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣የቋንቋ አወቃቀር ስህተት፣እና የስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተትቶች ናቸዉ፡፡ የስህተት ዓይነቶችም ተጠናቅረዉ የስህተት ብዛት፣ አማካይ የስህተት ብዛት፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ እና የትክክለኛነት ተዛምዷቸዉ ዝርዝር በሠንጠረዥ ተተንትኗል፡፡በተጨማሪም የግኝቶቹ ዉጠቶችም በገላጭ ስልት ተብራሪተዋል፡፡

### 3.5.1 የመጠይቆች አተናተን

ከተጠኚ ተማሪዎች እና ከአማርኛ መምህራን የተገኙ መጠይቆች ምላሽ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለዉ የሚታሰቡ መረጃዎችን ይጠቁማሉ፡፡መረጃዎቹም ገላጭ የአተናተን ስልትን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የዉጠት ማብራሪያ

### 4.1. የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሽክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች መለየትና ለስህተቶቹ መፈጸም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነዉ፡፡በዚህ ሂደትም በምዕራፍ አንድ የተጠቀሱትን የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥሯል፡፡

#### 4.1.1 በድርሰቶቹ ዉስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተት ብዛት

በሽክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች በመለየትና የስህተቶቹን ምንጮች ለማብራራት የድርሰቶቹ ብዛት፣ድርሰቶቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት፣አጠቃላይ የስህተት ብዛት ፣አማካይ ስህተት፣

አማካይ የስህተት ድግግሞሽ እና የትክክለኛነት ተዛምዷቸዉ ተተንትኗል፡

**ሠንጠረዥ 1.ድርሰቶቹ የተጻፉባቸዉ ቃላት ብዛት ፥የስህተት ብዛት በመቶኛ፥አማካይ የስህተት ድግግሞሽና ትክክለኛነት ተዛምዶ ዝርዝር መግለጫ**

| የድርሰቱ ዓይነት | የድርሰቶቹ ብዛት | ድርሰቶቹ የተጻፉበት ቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኛነት ተዛምዶ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት 1 | 40 | 8328 | 208.2 | 893 | 8.93 | 22.32 | 4.29 | 9.32 |
| ድርሰት 2 | 24 | 1572 | 65.5 | 605 | 6.05 | 25.20 | 9.30 | 1.60 |
| ድርሰት 1 ና 2 | 64 | 9900 | 273.7 | 1498 | 14.98 | 23.40 | 5.47 | 5.46 |

በሠንጠረዥ አንድ በቀረበዉ መረጃ መሰረት ተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ጊዜ በፃፏቸዉ 64 ድርሰቶች ዉስጥ ስህተቶቹ ተቆጥረዋል። ድርሰቶቹ የተፃፉት በ 9900 ቃላት ሲሆን አንድ ድርሰት በአማካይ 2737 ቃላት ይይዛል። በድርሰቶቹ ዉስጥ የተቆጠሩት ስህተቶች ብዛት 1498 ሲሆኑ በአንድ ድርሰት ዉስጥ በአማካይ 23.40 ስህተቶች ይገኛሉ።አንድ ድርሰት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ 5.47 ሲሆን የትክክለኛነት ተዛምዶዉ 5.46 እንደሆነ መረጃዉ ያስገነዝባል።

### 4.1.2 በድርሰቶቹ ዉስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች

ስህተቶቹ በዓይነት የተለዩት የቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ሲሆን በዚሁ መሰረት ጥናቱ መነሻ ያደረገባቸዉ የስህተት ዓይነቶችም፡- የቋንቋ አጠቃቀም፣የቋንቋ አወቃቀር እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸዉ።

የስህተት ዓይነቶቹ ከተጠናቀረዉ መረጃ አንፃር የስህተት ብዛት፣ አማካይ የስህተት ብዛት፣አማካይ የስህተት ድግግሞሽ እና የትክክለኛነት ተዛምዷቸዉ ዝርዝር መረጃ ከዚህ በታች ተቀምጠዋል።

**ሠንጠረዥ 2. በተማሪዎቹ ድርሰት ዉስጥ የተገኙ የስህተት ዓይነቶች ከስህተት ብዛት፣ ከስህተት ብዛት በመቶኛ ፣ከአማካይ ስህተት፣ከአማካይ ስህተት በመቶኛ እና ከትክክለኛነት ተዛምዶ አንጻር:-**

| ተ.ቁ | የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | | ድርሰት ሁለት | | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት | የትክክለኛነትተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይስህተት | ዐማካይስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነት ተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነት ተዛም |
| 1 | የቋንቋ አጠቃቀም | 571 | 63.94 | 14.27 | 2.74 | 14.59 | 370 | 61.15 | 15.41 | 5.64 | 4.24 | 941 | 62.54 | 14.84 | 4.19 | 9.45 |
| 2 | የቋንቋ አወቃቀር | 116 | 12.98 | 2.9 | 0.55 | 22.58 | 58 | 9.58 | 2.41 | 0.88 | 27.10 | 174 | 11.28 | 2.65 | 0.71 | 24.84 |
| 3 | የስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 218 | 24.41 | 5.45 | 1.04 | 50.22 | 135 | 22.31 | 5.62 | 2.06 | 11.64 | 353 | 23.36 | 5.53 | 1.55 | 30.93 |
| | ድምር | 905 | 101.33 | 22.62 | 4.33 | 87.39 | 563 | 93.04 | 23.44 | 8.58 | 42.98 | 1468 | 97.18 | 23.02 | 6.45 | 65.22 |

በሠንጠረዥ ሁለት በቀረበዉ መረጃ መሰረት በሁለቱም ድርሰቶች ከተለዩት የስህተት ዓይነቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረዉ በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ዉስጥ ነዉ።በአጠቃላይ ከተገኙት 1498 ስህቶች መካከል 941 የሚሆኑት በዚህ ስር የታዩ ስህተቶች ናቸዉ።ይህም በመቶኛ ሲሰላ 62.54% ሆኗል።በአንድ ድርሰት ዉስጥ የሚገኘዉ አማካ የስህተትመጠን 14.84 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹደግሞ4.19 ይሆናል።በተጨማሪም 9.45 የትክክለኛነት ተዛምዶ ዉጠት መረጃ እንደሆነ ያሳያል።

የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ደግሞ ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት መጠን የታየበት ምድብ ነዉ።በሁለቱ ዙር ከተጻፉት ድርሰቶች ዉስጥ የተገኘዉ ስህተት በመቶኛ ሲሰላ 23.36 % ይሆናል። አማካይ የስህተት መጠኑ 5.53 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 1.55 የሚሆን ነዉ። የትክክለኛነት ተዛምዶዉ ደግሞ 30.93 ነዉ።

የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ደግሞ ከ ቋንቋ አጠቃቀምና ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ የሚገኝ የመጨረሻ ደረጃ የስህተት ምድብ ነዉ። በዚህ የስህተት ምድብ ዉስጥ 87 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል። የዚሁ መቶኛ ስሌትም 11.28% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ 2.65 ሆኗል። አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 0.71 ሲሆን የትክክለኛነት ተዛምዶዉ 24.84 እንደ ሆነ መረጃዉ ያስገነዝባል።

### 4.1.2.1 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት

የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት በአጠቃላይ ከተገኙት 1204 ስህተቶች ዉስጥ 941 (62.54 %) ያህሉን ቁጥር የያዘ የስህተት ምድብ ነዉ። የዚህ የስህተት ምድብ የድግግሞሽ መጠን 4.19 ነዉ።

የአምላክ ሥራ(2008÷ 39) የመሰረት (2003÷ 44) ን ሀሳብ ዋቢ አድርጋ እነደ ጠቀሰችዉ ከመደበኛ የጽህፈት ሥርዓት ዉጪ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሀሳብን ከማስተላለፍ የሚገታ ብቻ ሳይሆን የመግባባት ሂደትንም የሚያደናቅፍ እንደሆነ ያስገነዝባል። በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ዉስጥ የተካተቱት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የቃላት አመራረጥ ፣ የቃላት ድግግሞሽ ፣የቃላት ጭመራ ፣የቃላት ግድፈት እና ተገቢ ሆሄያትን ካለመጠቀም የታዩ ስህተቶች ናቸዉ። እነዚህም እንደ ሚከተለዉ በሰንጠረዥ 3 ተዘርዝረዋል።

## ሠንጠረዥ 3- በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ዉስጥ የተፈጸሙ የስህተት ዓይነቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | | ድርሰት ሁለት | | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነ ተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነት ተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የስህተት ድግግሞሽ |
| 1. | የቃላት አመራረጥ | 90 | 17.40 | 2.25 | 0.43 | 92 | 73 | 7.84 | 3.04 | 1.11 | 21.53 | 163 | 12.62 | 2.64 | 0.77 | 57.03 |
| 2. | የቃላት ድግግሞሽ | 62 | 11.99 | 1.55 | 0.29 | 134.3 | 95 | 10.21 | 3.95 | 1.45 | 16.54 | 157 | 11.1 | 2.75 | 0.87 | 75.43 |
| 3. | የቃላት ጥመራ | 42 | 8.12 | 1.05 | 0.20 | 198.2 | 30 | 3.22 | 1.25 | 0.45 | 52.4 | 72 | 5.67 | 1.15 | 0.32 | 125.3 |
| 4. | የሆሄያት ግድፈት | 88 | 17.02 | 2.2 | 0.42 | 94.6 | 72 | 7.74 | 3 | 1.09 | 65.5 | 160 | 12.38 | 1.64 | 0.75 | 80.07 |
| 5. | ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ያለመጠቀም | 278 | 53.77 | 6.95 | 1.33 | 29.95 | 134 | 14.40 | 5.58 | 2.04 | 11.73 | 412 | 34.08 | 6.26 | 1.68 | 20.84 |
| | ድምር | 560 | 100 | 14 | 2.67 | 549.7 | 404 | 43.41 | 16.82 | 6.14 | 167.7 | 964 | 75.85 | 14.4 | 4.39 | 3.58 |

#### 4.1.2.1.1 ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ያለመጠቀም

በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ምድብ ዉስጥ ከቀረቡት 571 ስህተቶች ዉስጥ ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ባለመጠቀም 278 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል። ይህም በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ዉስጥ የመጀመሪያን ቁጥር ይይዛል። የስህተት መጠኑ በመቶኛ ሲሰላ 34.08 ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 6.26 ይሆናል። በዚህ ምድብ ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ መጠን 1.68 ይሆናል።

Byrene(1988÷1) እንዳስቀመጡት የቋንቋዉ ተናጋሪዎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ሆሄያት ሥርዓት ባለዉ መልኩ ተዋቅረዉ ቃላትን እንደሚመሰርቱ እና ሀሳብን በግልጽ ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ ገልጸዋል። ስለዚህ ሀሳቡን በጽሁፍ ለማስተላለፍ ሲፈለግ የቋንቋዉ ድምፀ ልሳናት የሚወክሉትን ፊደል በትክክል ለይቶ ማወቅና መጠቀም ያስፈልጋል።

ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ ከታዩት የሆሄያትን ተገቢ ቅርጽ ካለመጠቀም የተነሳ ከተስተዋሉት ስህተቶች መካከል ቀጥሎ ያሉት ለአብነት ቀርበዋል።

ሀ. … በተለቨሽን÷ በረድዎ እና በልዩ የሞባይል ምሰጆች … /06/

በሀምስ ፊደላት /ቴ/ና/ሌ/ መጻፍ የነበረባቸዉ በግዕዝ ፊደላት /ለ/ና/ተ/ ተጽፎ የመገኘት ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ. … አስፈርና አስግ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንሜለከታለን … /08/

በሳልስ /ሪ/ መጻፍ የነበረበት በሳድስ /ር/ የመጻፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. … ዮንፎርሙ ተቀደዉ የሚያስፋበትና … /08/

በካብዕ ፊደል /ዩ/ መጻፍ የነበረበት በሳብዕ ፊደል /ዮ/ የመፃፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

መ. …ሳይማር ባለዉ አኖኖርና አመለካከት በጣም … /05/

በድቃላ (ፍንጽቅ) ፊደላት መፃፍ የነበረባቸዉ በሳብዕ ፊደላት የመጻፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሠ. …በተሰቦቻችን ሰላም አገንቶ ተማሪዎችሁን … /04/

/ኘ/ን በ/ን/ ቀይሮ የመጻፋቸዉ ስህተት ሁለቱ ድምጾች በባህሪየ ፍጥረታቸዉ የሰርን ድምጾች በመሆናቸዉ ሁለቱን በዉል ካለመለየት የመነጨ ስህተት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም /ኣግግእኝእትእዉ/ ለማለት /አግግእንትኦ/ ያሉትም በሽክኛ ቋንቋ 22ቱ ተናባቢያንና 5ቱ አናባቢያን የድምጾች አጨራረስ በ‹‹o ኦ››ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ረ. … ስራ ሰርቶ ለመኖር በጣም አሰልች በመሆኑ … /05/

/ቺ/ ሳልስን በ/ች/ ሳድስ ተክቶ የመጻፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ. … ኩርጃን ከትምህርት በት እናስወግድ □ /03/

/ረ/ ግዕዝ በ/ር/ ሳድስ፣/ቤ/ ሀምስን በ/በ/ ግዕዝ ተክቶ የመጻፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሸ. …በተለያዩ ዘናዮችና በተለያዩ ነገሮች እየሰማንና እያየን ነዉ □ /06/

/ዜ/ ሀምስን በ/ዘ/ ግዕዝ ተክቶ የመጻፉ ስህተት በድምፆች አጠቃቀም ስለሆነ የስህተቱ ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ከለይ የተዘረዘሩት ስህተቶች የታዩበትን ሁኔታ ስንመለከት በ‹‹ሀ›› የተገለጸዉ በ ሀምስ ፊደላት ‹‹ቴ›› ና ‹‹ሴ›› መፃፍ የነበረባቸዉ በ‹‹ግዕዝ›› ፊደላት ‹‹ተ››ና ‹‹ሰ››ተጽፈዉ መገኘት የመጀመሪያዉ ሲሆን ሌላዉ ‹‹ዥ›› በ‹‹ሽ›› ተቀይሮ መፃፉ ነዉ□ ምክንያቱም ሁለቱም ድምፆች በመካነ ፍጥረታቸዉ ላንቃዊ÷ በበህሪየ ፍጥረታቸዉ ሹልክልክ ከመሆናቸዉ የተነሳ በምስስሎሽ ቀይሮ በመፃፍ የተከሰቱ ስህተቶች ናቸዉ□ በ‹‹ለ››ሳልስ ‹‹ ሪ›› መሆን የነበረበት በሳድስ ‹‹ር›› መፃፉ÷ በ ‹‹ሐ›› በካዕብ ፊደል‹‹ዩ›› መፃፍ የነበረበት በሳብዕ ‹‹ዮ›› መፃፉ ÷በ‹‹መ›› ዲቃላ ፊደላት (ፍንፅቆችን) ያለመጠቀም ስህተት ሲሆን በሳብዕ ፊደላት ‹‹ኖ››÷ ‹‹ኖ›› የተፃፉት በ‹‹ኗ››÷‹‹ ኗ›› መፃፍ ነበረባቸዉ □ በ ‹‹ሠ›› ‹‹አግኝተዉ ›› ለማለት ‹‹አገንቶ›› በማለት የጻፉትን ስንመለከት አንደኛ / ኘ/ ን በ/ን/ ቀይረዉ መጻፋቸዉ ሁለቱ ድምፆች በባህርየ ፍጥረታቸዉ የሰርን ድምፆች ከመሆናቸዉ የተነሳ ሁለቱን በዉል ካለመለየት የመነጨ ይመስላል □ ሁለተኛዉ /አግኝተዉ/ ለማለት / አግንቶ / ያሉትም እንደ ‹‹Ambassadder›› neechreraasha Ap’ari Bac’uri (2000) ‹‹ በሃያ ሁለት

ተነባቢያንና በአምስት አናባቢያን የሚጠሩ ድምፆች አጨራረሳቸዉ በአብዛኛዉ በ‹‹ o ›› ወይም ‹‹አ›› ድምፅ ነዉ ›› ይላሉ ።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተስተዋሉት የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶች እንደሚከተለዉ ተስተካክለዋል ።

ሀ. … በቴሌቪዥን÷በሬዲዮ እና በልዩ የሞባይል ምሰጆች …

ለ. … አስፈሪና አስጊ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንመለከታለን።

ሐ. … ዩኒፎርሙ ተቀደዉ የሚያሰፋበትና …

መ. …ሳይማር ባለዉ አኗኗርና አመለካከት በጣም …

ሠ. … ቤተሰቦቻችን ሰላም አግኝተዉ ተማሪዎቹን …

ረ. … ስራ ሰርቶ ለመኖር በጣም አሰልቺ በመሆኑ …

ሰ…. ኩረጃን ከትምህርት ቤት እናስወግድ ።

ሸ…. በተለያዩ ዜናዎችና በተለያዩ ነገሮች እየሰማንና እያየን ነዉ።

#### 4.1.2.1.2 በቃላት አመራረጥ ምክንያት የታዩ ስህተቶች

እንደ Raimes (1991; 7) አንድ ፀሀፊ የቋንቋዉን ቃላት በተገቢዉ ቦታ ካልተጠቀመ ሊተላለፍ የተፈለገዉ ሀሳብ ተድበስብሶ ሊቀር ይችላል። ምክንያቱም አንባቢዉ የሚገጥመውን ግልፅ ያልሆነ ሀሳብ ከጸሀፊዉ ጠይቆ መገንዘብ አይችልም ። ስለሆነም ተገቢ ቃላትን በተገቢ ቦታቸዉ መጠቀም የግድ ነዉ።

በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድቦች ዉስጥ ከቀረቡት ንዑሳን የስህተት ምድቦች ዉስጥ ሁለተኛዉ በቃላት አመራረጥ ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸዉ። በሠንጠረዥ 3 ከቀረበዉ መረጃ መገንዘብ እንደተቻለዉ በቋንቋ አጠቃቀም ስር ከተገኙት 964 አጠቃላይ ስህተቶች ዉስጥ 163(12 .62 %) በቃላት አመራረጥ ችግር ምክንያት የተፈጠሩ ናቸዉ ። አማካይ የስህተት መጠኑ 2.64 ሲሆን ድግግሞሹ ደግሞ 0.77 ነዉ። በአጠቃላይ በድርሰቶቹ 57.03 ቃላት ወይም ሀረጋት ዉስጥ በቃላት አመራረጥ ምክንያት አንድ ስህተት እንደምኖር የትክክለኛነት ተዛምዶ ዉጠት ያመለክታል።

ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ በቃላት አመራረጥ ምክንያት ከተስተዋሉ ስህተቶች ዉስጥ የሚከተሉት ተዘርዝረዋል□

ሀ … የትምህርት ጥቅም ስባል ደግሞ 1ኛ ገንዘብን ያስገኛል □ /05/

ተገቢዉን ቃል በተገቢ ቦታ ያለመጠቀም ስህተት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያትና በዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰተ ቢመስልም የቃላት አጠቃቀም ስህተት በአብዛኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ … በተለያዩ ዘናዮችና በተለያዩ ነገሮች እየሰመንና እያየን ነዉ □ /06/

የቃላት አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ … የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን□ /06/

የቃላት አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

መ … ጠንክሮ ካልሰራ ሁል ቀን በድህነት ጋር ነዉ የምጋጨዉ … /07/

የቃላት አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

ሠ… አስፈርና አስግ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንሜለከታለን … /08/

የቃላት አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

ረ … ስኮርጁ የሰዉን እዉቀት ስለምደግፉፍ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም□ /03/

የቃል አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ … በጣም ተፅዕኖ ላይ ያደረሰዉ ኩረጃ ስለሆነ … /03/

የቃል አጠቃቀም ስህተቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለዉ በዓረፍተ ነገሮቹ ዉስጥ በተገቢ ቦታቸዉ ተገቢ ቃላት ባለመግባታቸዉ እንዲተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት የደበዘዘበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ስለዚህ እንዲተላለፍ የተፈለገዉ ሀሳብ በሚከተለዉ መልኩ ቢስተካከል ተገቢ ነበር፡

ሀ … የትምህርት ጥቅም ሲባል ከብዙ በጥቂቱ 1ኛ ገንዘብ ያስገኛል፡

ለ … በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እየሰማንና እያየን ነዉ፡

ሐ … የኮሮና በሽታ አስከፊነትን እንረዳለን፡

መ … ጠንክሮ ካልሰራ በህይወት ዘመኑ ከድህነት ጋር ይዘልቃል ፡

ሠ … አስፈርና አስግ ጉዳይ እንደሆነ እንሚለከታለን፡

ረ …ስኮርጅ የሰዉን እዉቀት ስለሚተማመን ራሱን በራሱ ማስተዳድር አይችልም፡

ሰ … በጣም ተፅዕኖ ያስከተለዉ ኩረጃ ስለሆነ …

### 4.1.2.1.3 በግድፈት ምክንያት የተስተዋሉ ስህተቶች

ግድፈት በአፈፃጸም ችግር ስህተት ዉስጥ የሚካተት ሲሆን ይህም በአንድ ቃል ፥ሀረግ ወይም ዓረፍተ ነገር ዉስጥ መገኘት ከሚገባቸዉ ቅንጅቶች ዉስጥ የተወሰኑት ድምፆች ፥

ቃላት ወይም ሀረጋት ሳይገኙ መቅረታቸዉን የሚመለከት ነዉ፡እንደ Negara (1983 ;35-36) እነዚህን ግድፈቶች አፍ ፈቶችም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተናጋሪዎች ሊፈጽሟቸዉ እንደሚችሉና ስህተቶቹም የሚፈጸሙት ቋንቋዉን ባለማወቅ ሳይሆን በችኮላ፥በስሜት ወይም ጭንቀት ዉስጥ ሆኖ በመናገር ወይም በመጻፍ አሊያም በግዴለሽት ነዉ ይላሉ፡

በጥናቱ መረጃ መሰረት ተጠኚ ተማሪዎቹ በድርሰቶቻቸዉ ዉስጥ የገደፏቸዉ ድምጾችና ቃላት በመኖራቸዉ የጽሁፉ መልዕክት እንደ ደበዘዘ ተስተዉሏል፡ በድርሰቶቹ ዉስጥ ከተገኙት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 160 ያህሉ በዚህ የስህተት ምድብ ዉስጥ የተገኙ ናቸዉ፡ይህ ቁጥር በመቶኛ 12. 38% ያህሉን ቁጥር ይዟል፡ አማካይ ስህተቱ 1.64 ሲሆን

ድግግሞሽ መጠኑ 0.75% እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡ በአጠቃላይ በድርሰቶቹ 80.07 ቃላት ወይም ሀረጋት ዉስጥ አንድ በግድፈት ምክንያት የተከሰተ አንድ ስህተት እንዳለየትክክለኛነት ተዛመዶ ዉጤት ያመለክታል፡

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ ከተስተዋሉት የግድፈት ስህተቶች ዉስጥ የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል

… በሠላም አስተማር የሚሰጠዉን ትም(ህ ) ርት ተከታተሉ … /04/

Dulay et.al.(1982;138-139) በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳላቸዉ ያብራሩትን ምዕራፍ ሁለት ስር የተጠቀሰዉን መነሻ በማድረግ ግድፈት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… ተማርም ሰላም አ(ጥ) ቶ አስተማርም ሰላም አ(ጥ) ቶ በተጨነቀ … /04/

የ/ጥ/ ድምጽ መገደፍ የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… ስለዝ (ህ) የሰላም ፍቅር ይሻለኛል … /04/

የ/ህ/ ድምጽ መገደፍ የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… በሀገራች (ን )ም ሆነ በመንደራች (ን ) እጅግ … /08/

የ/ን/ ድምጽ መገደፍ የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… አኖኖርና አመለካከት በጣም የ (ተ )ሻለ ( ነ )ዉ  /05/

የድምጾቹ ግድፈት የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… ተማርዉ መርዳ (ት ) አ( ይ )ችሉም  /08/

የድምጾቹ ግድፈት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

… መፍት (ሄ) ዉ ጠንክሮ መስራትና ደህነትን ማጥፋት … /07/

የ/ሄ/ ድምጽ ግድፈት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፣ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

### 4.1.2.1.4 የቃላት ድግግሞሽ

በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ስር ከቀረቡ ንዑሳን የስህተት ምድቦች ዉስጥ አራተኛዉን ደረጃ ይዞ የሚገኘዉ የቃላት ድግግሞሽ ነዉ በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ሆን ተብሎ የሚደረግ ድግግሞሽ ማስተላለፍ የተፈለገዉን ጭብጥ እንደሚያጎላ ሁሉ ሳይፈለጉ የሚደረጉ ድግግሞሾች እንዲተላለፍ የተፈለገዉን መልዕክት ያደበዝዛሉ 

በተጠኚ ተማርዎቹ ድርሰቶች ዉስጥ የቃላት ድግግሞሽ ስህተት ቁጥር 157 ያህሉን ቁጥር ይዟል ። ይህ የስህተት መጠን በመቶኛ ሲሰላ 11.1% ይሆናል። አማካይ የስህተት መጠኑ 2. 75 ሲሆን ድግግሞሹ ደግሞ 0.87 ነዉ። በአጠቃላይ በድርሰቶቹ 75.43 ቃላት ወይም ሀረጋት ዉስጥ በቃላት ድግግሞሽ ምክንያት አንድ ስህተት እንደሚኖር የትክክለኛነት ተዛምዶ ዉጠት ያመለክታል።

በድርሰቶቻቸዉ ዉስጥ በድግግሞሽ ምክንያት ከተስተዋሉት ስህተቶች የሚከተሉት በምሳሌነት ቀርበዋል ።

… ስራ ባለመስራታቸዉ ድህነትን በራሳቸዉ ላይ ድህነትን ይጋብዛሉ ። /07/

በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳላቸዉ ምሁራን የጠቆሙትን መነሻ በማድረግ ድግግሞሽም በዚሁ ዉስጥ ይካተታል፡፡ስለዚህ ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ይመስላል፡፡

… ድህነቱ ካልጠፋ ለትዉልድ ስለምተላለፍ ድህነቱ ለትዉልድ አልፎ ትዉልድ እንዳይጎዳ … /07/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ይመስላል፡፡

… በዝሁ የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን። /06/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ይመስላል፡፡

… ኩረጃን ከትምህርት በት እናስወግድ ስንል ሀገራቱን ያበላሸ ወይም ያጠፋ ኩረጃ ነዉ። /03/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ይመስላል፡፡

… ሰዎች ትምህርት ላይ መቀለድ የለባችሁም ለምን ከተባሌ የሁሉ በር ከፋች የሆነዉ ትምህርት ነዉ። /05/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ይመስላል፡፡

### 4.1.2.1.5. የቃላት ጭመራ(እከላ)

በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድቦች ዉስጥ ከቀረቡት አምስት ንዑሳን የስህተት ምድቦች ዉስጥ የመጨረሻዉን ቁጥር የያዘዉ አላስፈላጊ የቃላት ጭመራ ነዉ። በቃላት ጭመራ

የተከሰቱ የስህተት ቁጥር 72 ያህሉን ይዟል የስህተት መጠን በመቶኛ ሲሰላ 5.67%ይሆናል አማካይ የስህተት መጠኑ 1.15 ሲሆን ድግግሞሹ ደግሞ 0.32 ነዉ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ በጭመራ ምክንያቶች ከተስተዋሉት ስህተቶች መካከል የምከተሉት ቀርበዋል 

ሀ … ይህ ኮሮና በሽታ በህብረተሰቡ ላይ አስግ ችግር እያደረሰ መሆኑ … /06/

በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳላቸዉ ምሁራን የጠቆሙትን መነሻ በማድረግ ጭመራንም በዚሁ ዉስጥ ማካተት ይቻላል፡፡ስለዚህ የስህተቱ ምንጭ የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ … አስተማርያች ሰላም አገኝቶ ተማርዎችሁን ማስተማር ቻሉ … /04/

የ/ሁ/ ድምጽ መጨመር የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ … አንድ ተማር ትህምህርቱን መማር ስጀምር … /08/

የ/ህ/ ድምጽ መጨመር የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

መ … ዮንፎርሙ ተቀደዉ የምያሰፋበትና ሻይ ቡና የምልበት /08/

የ/ዉ/ ድምጽ መጨመር የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ሠ … በዝሁ የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን  /06/

- ተቀራራቢ ፍች ያላቸዉን ቃላት መጠቀሙ የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ዉስጥ እንደሚታየዉ እንድሁ የታከሉት አላስፈላጊ ድምጾችና ቃላት የዓረፍተ ነገሮቹን መልዕክት አድበስብሰዋል የተፈጠሩትን ስህተቶች እንደሚከተለዉ ማስተካከል ይቻል ነበር

… ኮሮና በሽታ በህብረተሰቡ ላይ ችግር እያደረሰ መሆኑ …
… አስተማርያች ሠላም አገኝቶ ተማርዎችን ማስተማር ቻሉ …
… አንድ ተማር ትምህርቱን መማር ስጀምር …
… ዮንፎርሙ ተቀዶ የምያሰፋበትና ሻይ ቡና የምልበት …
… በዝሁ የኮሮና በሽታ ቀዉስ እንረዳለን …

#### 4.1.2.2. የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች

ሥርዓተ ነጥቦች የአንድ ጽሁፍ መሪ ምልክቶች እንደመሆናቸዉ መጠን የጽሁፉን መልዕክት ግልጽ ለማድረግ ይጠቅማሉ። ነገር ግን ተገቢዉን ሥርዓተ ነጥብ መጠቀም በሚገባን ቦታ ካልተጠቀምን ለማስተላለፍ የሚንፈልገዉ ሀሳብ በአግባቡ እንዳይደርስ ይገታል።

በአንድ ጽሁፍ  ዉስጥ ሥርዓተ ነጥብ የምንጠቀመዉ ለሁለት አላማ ነዉ። አንደኛዉ በሚንጽፈዉ ጽሁፍ ዉስጥ ያሉ ቃላት ፣ሀረጋትና ዓረፍተነገሮች አሰዳደር ሥርዓትን የጠበቁና ተነባቢ እንድሆኑ ለማድረግ ፤ሁለተኛዉ ዓላማ ደግሞ የጻፍነዉ ጽሁፍ መልዕክት ለአንባቢያን በተገቢዉ መንገድ እንድደርሰዉ ለማድረግ ነዉ።ነገር ግን በተገቢዉ ቦታ ተገቢዉን ሥርዓተ ነጥብ አለመጠቀም ወይም ፈጽሞሥርዓተ ነጥብ አለመጠቀም የጽሁፋችን መልዕክት ባሰብነዉ መልኩ ለአንባቢ እንዳይደርስ ምክንያት ይሆናል፤ ለአንባቢም ግራ ያጋባል።ስለዝህ ጸሀፊዉ የጻፈዉን መልዕክት አንባቢ እንዲረዳለት ለማድረግ በተገቢዉ ቦታ ተገቢ ሥርዓተ ነጥቦችን መጠቀም ይኖርበታል ።ይህ ካልሆነ ግን የአንባቢን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ እንደሚችል dulay.et.al (1982;137) ገልጸዋል።

በዚህ ጥናት ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች ቀጥሎ 353 ያህል ቁጥር ያለዉ የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ስህተት ነዉ ።

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ በብዛት የተስተዋሉት በቅደም ተከተላቸዉ መሰረት የነጠላ ሠረዝ ፣ የአራት ነጥብ፣የድርብ ሠረዝ፣ የትዕምርተ አንክሮ ፣የጥያቄ ምልክት እና የሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ዋናዋና የስህተት ዓይነቶች ናቸዉ።

## ሠንጠረዥ 4 በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ የተፈጸሙ የስህተት ዓይነቶች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | | ድርሰት ሁለት | | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነ ተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የትክክለኛነት ተዛምዶ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | አማካይ ስህተት በመቶኛ | የስህተት ድግግሞሽ |
| 1 | አራትነጥብ | 51 | 11.88 | 1.27 | 0.24 | 163.29 | 60 | 6.45 | 2.12 | 0.91 | 26.2 | 111 | 9.16 | 1.69 | 0.57 | 0.94 |
| 2 | ድርብ ሠረዝ | 36 | 8.39 | 0.9 | 0.17 | 231.3 | 16 | 1.72 | 0.66 | 0.24 | 98.25 | 52 | 5.05 | 0.78 | 0.47 | 1.64 |
| 3 | ነጠላ ሠረዝ | 108 | 25.17 | 2.7 | 0.51 | 77.11 | 46 | 4.96 | 0.20 | 0.70 | 34.17 | 154 | 15.05 | 1.45 | 0.6 | 0.55 |
| 4 | ትዕምርተ አንክሮ (ቃለ አጋኖ) | 11 | 2.56 | 0.27 | 0.05 | 757.09 | 4 | 0.43 | 0.16 | 0.06 | 393 | 15 | 1.49 | 0.21 | 2 | 5.75 |
| 5 | ጥያቄ ምልክት | 7 | 1.63 | 0.17 | 0.03 | 1189.7 | 6 | 0.64 | 0.25 | 0.09 | 262 | 13 | 1.13 | 0.4 | 0.06 | 7.25 |
| 6 | ሁለት ነጥብ ከሠረዝ | 5 | 1.16 | 0.12 | 0.02 | 1665.6 | 3 | 0.32 | 0.32 | 0.04 | 524 | 8 | 1.48 | 0.22 | 0.7 | 10.94 |
| | ድምር | 218 | 50.79 | 5.43 | 1.02 | 40.83 | 135 | 14.5 | 3.71 | 2.04 | 13.37 | 353 | 33.36 | 25.35 | 4.4 | 27.10 |

#### 4.1.2.2.1 የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ አራት መረጃ መሰረት በሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ስህተት ዉስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛዉን ቁጥር ይዞ ይገኛል፡በድርሰቶች ዉስጥ ከታዩት 1498 ስህተቶች መካከል 353 ያህሉ በሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም የስህተትምድብ ዉስጥ የሚገኙ ሲሆን 154 ያህሉ በነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት የተመዘገቡ ናቸዉ፡የዚህ ቁጥር ቁጥር መቶኛ 15.05 % ሲሆን አማካይ ስህተቱ

1.45 ነዉ፡ በየመቶ ቃላቱ ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 0.55 ይሆናል

በዚህ የስህተት ምድብ ዉስጥ የተስተዋሉ ስህተቶች አብዛኞቹ ነጠላ ሠረዝ በመግደፍ የታዩ ናቸዉ፡

*ሀ. ሠላም በሀገራችን ኖሮ ( ) ተማርዎችም ሠላም አገንቶ( ) ትምህርትን ተማሩ … /04/*

*ይህ ነጠላ ሠረዝን የዉስየመግደፉ ምክንያት ጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡*

*ለ. …እበት ላሉት በተሰቦቻችን ሰላም አገኝቶ( ) የምያስተምር አስተማሪያች ሠላም አገኝቶ ( ) ተማሪዎቹን ማስተማር ቻሉ… /04/*

*ይህ ነጠላ ሰረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡*

*ሐ. …ባለፎ ሠላም አቶ ( ) ተማርም ሠላም አቶ ( ) አስተማርም ሰላም አቶ( ) በተጨነቁት ጊዜ… /04/*

*ይህ ነጠላ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡*

*መ. … እንዲሁም የሚበላበትን ( ) የምጠጣበትን ( ) እስክብርቶ የምገዛበትን ( ) ዮንፎርሙ ተቀደዉ የምያሰፋበት … /08/*

*ይህ ነጠላ ሰረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡*

ሠ. … ከትምህርታችን ገበታ ( ) ከልዩ ስራችን ( ) ወደ ኃላ እየመለሰን … /06/

ይህ ነጠላ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ረ. … በተሀይማኖትን ( ) መሸጥ መግዛትን ( ) ትራንስፖርት ጉዞን ( ) ሰዉን ከሰው ( ) ዘመድን ከዘመድ ( ) ባሉን ከምስጥ ( ) ልጆችን ከአባት () እናትን ከልጆች ( ) ሀገርን ከሀገር ( ) ሰዉን ከልማት ( ) በረሀብ ሰዉ እንድያልቅ( ) የገብ ምንጭን የያዘዉ ቀላል አይመስላች ኮቪድ19 /01/

ይህ ነጠላ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

- ከምሳሌዎቹ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተጠኚ ተማርዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ በዓረፍተነገር ዉስጥ ተደርድረዉ የሚገቡትን ቃላት ፣ሀረጋት እና ሌሎችን ሀሳቦች ለመለየት የሚያገለግለዉን ነጠላ ሠረዝ በመግደፋቸዉ የተስተዋሉ ስህተቶች ናቸዉ፡፡

### 4.1.2.2.2. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ አራት መረጃ መሰረት በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ዉስጥ ከተዘረዘሩት ነዑሳን የስህተት ምድቦች የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ ያለዉን ደረጃ የያዘ ነዉ፡፡ ይህም በድርሰቶቹ ዉስጥ ከታዩት 1498 ስህተቶች 111 ያህሉ በአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት የተመዘገቡ ናቸዉ፡፡ የዝህ ቁጥር መቶኛ 9.16% ሲሆን አማካይ ስህተቱ 1.69 ነዉ፡፡ በእየ መቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ደግግሞሽ ደግሞ 0.94 ይሆናል ፡፡ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ አራት ነጥብ መጠቀም ሲገባቸዉ ባለመጠቀማቸዉ ከፈጸሙት ስህተቶች መካከል ለአብነት ያህል :-

ሀ. … ድህነቱ ለትዉልድ አልፎ ትዉልድ እንዳይጎዳ መጠንቀቅ ይኖርብናል ( ) /07/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ለ. … ሠላም ለሰዉ ልጅ ባይኖር የሰዉ ልጅ በደህንነት አይኖርም ነበር ( ) /04/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሐ. … ስለዝ የሰላም ፍቅር ይሻለኛል( ) /04/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

መ. … እጅግ በጣም አስፈሪና አስግ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንሜለከታለን ( ) /08/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሠ. … ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም ( ) /03/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ረ. … ካሁኑ ኩረጃን ማቆም አለብን ( ) /03/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሰ. … ኮሮና ቫይረስ ወይም ኮቪድ 19 ተብሎ ይታወቃል ( ) /01/

ይህ አራት ነጥብን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ከምሳሌዎቹ መረዳት እንደምቻለዉ ተጠኚ ተማርዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ የአንድ ሀሳብ መቋጫ ወይም መግቻ አመላካች የሆነዉን አራት ነጥብ ባለመጠቀም የተከሰቱ ስህተቶች ናቸዉ፡፡

#### 4.1.2.2.3 የድርብ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ አራት መረጃ መሰረት በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ዉስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የድርብ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ሦስተኛዉን ደረጃ የያዘ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነዉ፡፡ ይህም በድርሰቶች ዉስጥ ከታዩት 1498 ስህተቶች 52 ያህሉ በድርብ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተት የተመዘገቡ

ስህተቶች ናቸዉ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 5.05 %ሲሆን አማካይ ስህተቱ 0.78 %ነዉ በየመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ1.64 ይሆናል 

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ ድርብ ሠረዝ መጠቀም ሲገባቸዉ ከገደፏቸዉ ስህተቶች መካከል ለምሳሌ ያህል:-

ሀ. … ሁል ቀን በድህነት ጋር ነዉ የሚጋጨዉ ( ) ስለዝህ አንድ ሰዉ … /07/

ይህ ድርብ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ለ. … ሰዉ በህይወት እስካለ ድረስ ጠንክሮ መስራት ይጠበቅበታል ( ) ስለዝህ አንዳንድ ሰዎች … /07/

ይህ ድርብ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሐ. … ተማሪዎችሁን ማስተማር ቻሉ ( ) ተማርዎቹም በሰላም አስተማር … /04/

ይህ ድርብ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

መ. … የኑሮ ዉድነት አጋጠመዉ ( ) እንዲሁም የሚበላበትን /08/

ይህ ድርብ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሠ. …. የሚኮርጅ ሰዉ ራሱን ተማምኖ አይኖርም ( ) ሲኮርጂ የሰዉን ዕዉቀት /03/

ይህ ድርብ ሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ረ. … ገንዘብን የስገኛል ( ) ሁለተኛ ደግሞ ዕዉቀት ያስጨብጣል ( ) ስልም ደግሞ… /05/

ይህ ድርብ ሥረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሰ. … አንድ ሰዉ ራሱን ችሎአል ( ) ስንል ራሱን በራሱ ስያስተዳድር ነዉ። /03/

ይህ ድርብ ሥረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ከምሳሌዎቹ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠኚ ተማርዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ የሀሳብ ቁርኝት ያላቸዉ ዓረፍተ ነገሮችን አጣምሮ ለማቅረብ የሚያገለግለዉን ድርብ ሥረዝ ባለመጠቀማቸዉ ምክንያት የተከሰቱ ስህተቶች ናቸዉ።

### 4.1.2.2.4 . የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ አራት መረጃ መሰረት በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ዉስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን የስህት ምድቦች የጥያቄምልክት አጠቃቀም ስህተት አምስተኛዉን ደረጃ የያዘ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነዉ ። ይህም በድርሰቶቹ ዉስጥ ከታዩት 1498 ስህተቶች 13 ያህሉ በጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት የተመዘገቡ ስህተቶች ናቸዉ።

ይህም በመቶኛ ሲሰላ 1.13 % ሲሆን አማካይ ስህተቱ 0.21 % ነዉ።በየመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ ሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 7.25 % ይሆናል።

ተጠኚ ተማሪዎች በጽሁፋቸዉ ዉስጥ ጥያቄ ምልክት መጠቀም ሲገባቸዉ የገደፏቸዉን ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል።

ሀ. … አንዳንድ ሰዎች ትምህርት ላይ መቀለድ የለባቸዉም ለምን (? ) ከቴባሌ… /05/

ይህ ጥያቄ ምልክትን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ለ. … ራሱን ተማምኖ በምሰራበት ሰዓት በራሱ ብቻ መስራት አለበት ለምን ( ) ከተባለ የሰዉን የሚፈልግ … /03/

ይህ ጥያቄ ምልክትን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ከምሳሌዎቹ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ሲያጋጥም የጥያቄ ምልክት መጠቀም ሲገባቸዉ የገደፏቸዉ ስህተቶ ች ናቸዉ 

#### 4.1.2.2.5 የሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ አራት መረጃ መሰረት በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ዉስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን የስህተት ምድቦች የሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተት ነዉ

ይህም በድርሰቶቹ ዉስጥ ከታዩት 1498 ስህተቶች 8 ያህሉ በሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተት የተመዘገቡ ስህተቶች ናቸዉይህም በመቶኛ ሲሰላ 1.48 % ሲሆን አማካይ ስህተቱ 0.22 % ነዉ በመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 10.94 % ይሆናል 

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ ሁለት ነጥብ ከሠረዝ መጠቀም ሲደባቸዉ የገደፏቸዉን ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል

ሀ. …የትምህርት ጥቅም ስባል ደግሞ ( ) 1ኛ ገንዘብን ያስገኛል÷ 2ኛ… /05/

ይህ ሁለት ነጥብ ከሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ለ. … ድህነት ( ) ማለት የአንድ ሰዉ ድካምን ይገልጻል  /07/

ይህ ሁለት ነጥብ ከሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሐ. … የኮሮና በሽታ እየቀጠለ እንዳለ እኛ ደግሞ በፍረሀትና በስጋት ዉስጥ ነንምክንያቱም ( ) ከዝህ በፊት … /06/

ይህ ሁለት ነጥብ ከሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

መ. … ኩረጃ ( ) ኩረጃ በተመለከተ የሚኮርጅ ሰዉ ራሱን ተማምኖ አይኖርም … /03/

ይህ ሁለት ነጥብ ከሠረዝን የመግደፉ ምክንያት የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ከምሳሌዎቹ መረዳት እንደምቻለዉ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጽሁፋቸዉ ዉስጥ የአንድ ዓረፍተ ነገር ሀሳብ ከማብቃቱ በፊት በዝርዝር የሚቀርቡ ነጥቦች መኖራቸዉን ለማመልከት መጠቀም የነበረባቸዉን ሁለት ነጥብ ከሠረዝ ሥርዓተ ነጥብ ገድፈዋል

## 4.1.2.3. በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋሰዉ )ስር የታዩ ንዑሳን ስህተቶች

በጽሁፍ የሚተላለፍ መልዕክት በጥንቃቄ የተዋቀሩ ዓረፍተ ነገሮችን ልይዝ ይገባል Widdowson (1976;118) ሲገልጹ በጽሁፍ የሚገለጽ ሀሳብ በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለአንባቢ ሊተላለፍ የሚችለዉ ሰዋሰዋዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ሲጻፍ ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ  በሠንጠረዥ ሁለት ላይ በቀረበዉ መረጃ መሰረት በአብይ የስህተት ምድብ ከቀረቡት ሦስት የስህተት ዓይነቶች መካከል በስህተት ብዛቱ ሦስተኛዉን ደረጃ የያዘዉ የቋንቋ አወቃቀር (ሰዋሰው) ስህተት ነዉ ይህ የስህተት ምድብ ባጠቃላይ ከተገኙ 1468 ስህተቶች መካከል 174 ያህል ቁጥር ይዟል  ይህም በመቶኛ ሲሰላ 11.28 % ነዉ አማካይ የስህተት መጠኑ 2.65 ሲሆን በመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ መጠን 0.71 ነዉ 

## ሠንጠረዥ 5  በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ዉስጥ የተገኙ የስህተት ዓይነቶች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድ እና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | ስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | የስህተት | አማካይ ስህተት | ስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | ስህተት ድግግሞሽ |
| 1 | የዓረፍተነገር ስሙምነት ያለመኖር | 35 | 8.15 | 0.87 | 0.16 | 36 | 3.87 | 1.5 | 0.54 | 33.5 | 6.01 | 1.18 | 0.7 |
| 2 | የቃላት አጠቃቀም | 34 | 7.92 | 0.85 | 0.16 | 1 | 0.10 | 0.04 | 0.01 | 17.5 | 4.01 | 0.44 | 0.08 |
| 3 | የመስተዋድድ እና የተሳቢ አጠቃቀም | 17 | 3.96 | 0.42 | 0.08 | 18 | 1.93 | 0.75 | 0.27 | 17.5 | 2.94 | 0.17 | 0.17 |
| | ድምር | 86 | 12.03 | 2.14 | 0.4 | 55 | 5.9 | 2.29 | 0.82 | 70.5 | 12.96 | 1.79 | 0.95 |

#### 4.1.2.3.1 የዓረፍተ ነገር ስሙምነት አለመኖር

በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ስር ከቀረቡት ንዑሳን የስህተት ምድቦች መካከል የመጀመሪያዉን ደረጃ የያዘዉ የዓረፍተ ነገር ስሙምነት አለመኖር ነዉ  በአብይ የስህተት ምድብ ከተገኙት 174 ስህተቶች ዉስጥ 35 ያህሉ በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ የተፈጸሙ ስህተቶች ናቸዉ በመቶኛ ሲሰላ 6.01 % ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 1.18 ሆኗል  በመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ መጠኑ 0.7 ነዉ በዓረፍተ ነገር ስሙምነት ያለመኖር ምክንያት ከታዩ ስህተቶች ዉስጥ ቀጥሎ ያሉት ለአብነት ቀርበዋል 

ሀ. … የተማሪዉ እናትና አባታቸዉ እንዳጋጣሚ በኑሮ ዉድነት ከተመቱ ይህ ተማርዉ መርዳ አልቻለም /08/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የተከሰተ ይመስላል፡፡

ለ. … እንደ አጋጣሚ በኑሮ ዉድነት ከተመቱ ይህ ተማርዉ መርዳ አለቻለም ስለዝህ ይህ ተማር በኑሮ ዉድነት ምክንያት ትምህርቱን አቋረጠ /08/

ስህተቱ ከዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. … ተማርዎችም ሠላም አገኝቶ ትምህርትን ተማሩ /04/

ስህተቱ ከዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

መ. … አገራችን ሠላም አታ መንግስት ሠላም አታ በተጨነቀች ጊዜ ፈጣር ሰላሙን አመቶ … /04/

ስህተቱ ከዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

ሠ. ለሰዉ ልጅ ደህንነትን ሰጠ ስለዝ የሰላም ፍቅር ይሻለኛል  /04/

ስህተቱ ከዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

በአንደኛ ምሳሌላይ የተከሰተዉ ስህተት ‹‹የተማርዉ እናትና አባታቸዉ ››በሚለዉ ስማዊ ሀረግ ዉስጥ የቁጥር ስህተት ዉስጥ የቁጥር ስህተት ይታያል

ይህም ‹‹ተማርዉ››ነጠላ ቁጥር ሆኖ ሳለ ‹‹አባታቸዉ ››ለብዙ ቁጥር ባለቤት የተገለጸ ነዉ።ይህም ሲስተካከል ‹‹የተማርዉ እናትናአባት ይሆናል›› በዚሁ ዓረፍነገር ‹‹አለቻለም››የሚለው ግስ መቋጨት የሚገባዉ በነጠላ ቁጥር አመልካች በሆነዉ ‹‹አይችሉም›› መሆን ነበረበት

በሁለተኛዉ ዓረፍተነገር የሚታየዉ ስህተትደግሞ የጊዜ አለመጣጣም ነዉ፡፡ ማለትም የኑሮ ዉድነት ካጋጠመ የሚል የትንቢያ ሀሳብ እየቀረበ ባለበት በማሰሪያ አንቀጹ ላይ ‹‹አቋረጠ›› የሚል የሀላፊ ጊዜ አመልካች ግስ መግባት አልነበረበትም፤ስለዚህ የዓረፍተነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ መሆን ያለበት ‹‹ያቋርጣል››የሚል በ3ኛ መደብ ÷ተባዕት ጾታ ÷ነጠላ ቁጥር የትንቢያ ቃል መሆን ነበረበት

በሦስተኛዉ ዓረፍተ ነገር የሚታዉ ስህተት ደግሞ የቁጥር አለመስማማት ነዉ።ይህም ባለቤቱ ላይ‹‹ተማሪዎች ››በሚል ብዙቁጥር አመልካች 3ኛመደብ የጀመረ ቢሆንም በተሳቢዉ ላይ ግን ‹‹አገኝቶ ››የሚል ነጠላ ቁጥር÷እሱ 3ኛ መደብ መሆን አልነበረበትም፤ስለዚህ መሆን የነበረበት‹‹አግኝተዉ››የሚል የብዙ ቁጥር÷3ኛመደብ ÷እነሱ መሆን ነበረበት፡፡ ‹‹ትምህርትን›› የሚለዉ ተሳቢም‹‹ትምህርታቸዉን››በሚል 3ኛ መደብ÷ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ቢፃፍ የተሻለ ይሆናል፡፡ ‹‹ተማሩ›› የሚለዉ ግስም ‹‹ይማራሉ››ተብሎ መጻፍ ነበረበት፡፡

በአራተኛዉ ዓረፍተነገር የሚታዩት ስህተቶች የቁጥር÷የጾታ ያለመስማማት እና አጣማሪዎችን ያለመጠቀም ስህተት ናቸዉ፡፡ ይህም ‹‹ሀገራችን ሰላም አታ÷መንግስት ሰላም አታ በተጨነቀች ጊዜ›› በማለት ‹‹ፈጣሪ ሰላሙን አመቶ ››የሚለዉን ያላሰረ ጥገኛ ግስ እንዲያስር አድርጎ ‹‹ፈጣሪ ሰላሙን አመጣ›› በሚለዉ ማስተካከል ይቻላል

በአምስተኛዉ ዓረፍተነገር የሚታየዉ ስህተት ደግሞ የቁጥር÷የመደብ እና አጣማሪዎችን ያለመጠቀም ስህተት ነዉ ይህም ‹‹የሠላም ፍቅር ይሻለኛል›› የምለዉ ዘርፍ አመልካች ‹‹የ›› ሠላም በምለዉ ቃል ላይ መታከሉ ያለአግባብ ስለሆነ ‹‹የ›› ን ገድፈን አጣማሪ በመጠቀም ‹‹ሠላም እና ፍቅር›› በማለት ‹‹ይሻለኛል›› በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የተገለጸዉን ‹‹ይሻለናል››በማለት በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ማስተካከሉ የተሻለ ይሆናል

#### 4.1.2.3.2 የቃላት አጠቃቀም ስህተት

በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ስር ከቀረቡት ንዑሳን የስህተት ምድቦች መካከል ሁለተኛዉን ደረጃ የያዘዉ የቃላት አጠቃቀም ስህተት ነዉ። በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ዉስጥ 17 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል ። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 2.94 % ሲሆን በአንድ ድርሰት የሚገኘዉ አማካይ ስህተት 0.44 % ሆኗል።በመቶ ቃላት ዉስጥ ያለዉ ድግግሞሽ መጠን ደግሞ 0.08 ነዉ። በዚህ የስህተት ምድብ ዉስጥ ለተከሰቱ ስህተቶች መነሻ የሆነዉ ቃላትን በተገቢዉ መንገድ በዓረፍተ ነገር ዉስጥ ባለመጠቀም የታዩ ናቸዉ።

በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ዉስጥ ከተገኙ ስህተቶች መካከል ለአብነት ያህል:-

ሀ. … በተለያዩ ዘናዮችና በተለያዩ ነገሮች እየሰማንና እያየን ነዉ ። /06/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ እንደተከሰተ ይገመታል፡፡

ለ. … በልዩ የሞባይል ምሰጆች እያየን መሆኑ… /06/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ እንደተከሰተ ይገመታል፡፡

ሐ. … የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን። /06/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ እንደተከሰተ ይገመታል፡፡

መ… ስኮርጅ የሰዉን እዉቀት ስለምደግፍ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም። /03/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ እንደተከሰተ ይገመታል፡፡

ምሳሌ አንድ የቀረበዉ ዓረፍተ ነገር ‹‹በተለያዩ ነገሮች ››ከሚባል ይልቅ ‹‹ከመገናኛ ብዙሀን ››ቢባል ‹‹ዘናዮች እየሰማንና እያየን›› የሚለዉ ደግሞ ‹‹የሚናገኛቸዉ መረጃዎች ›› ተብሎ በተገቢ ቃላት ቢጻፍ የተሻለ ነበር ።

በምሳሌ ሁለት በቀረበዉ ዓረፍተ ነገር ዉስጥ ደግሞ የእንግሊዘኛዉን የቃላት አጠቃቀም በቀጥታ ወደ አማርኛዉ ተጠቅመዋል፡፡ ይህም ‹‹የሞባይል ምሰጆች›› የምለዉ ‹‹የሞባይል መልዕክቶች ››ተብሎ በአማርኛዉ የቃል አጠቃቀም መጻፍ ነበረበት።

በምሳሌ ሦስት በዓረፍተነገሩ ዉስጥ የገቡት ቃላት ተቀራራቢ መልዕክት ያላቸዉ እና አንድን ጉዳይ ለመግለጽ የተደረደሩ ናቸዉ። ስለዚህ ‹‹ቀዉስ ጉዳት›› ከማለት ‹‹ቀዉስ›› ወይም ‹‹ጉዳት››ተብሎ በአንደኛዉ ብቻ ቢገለጽ የተሻለ ነዉ።

በምሳሌ አራት በቀረበዉ ዓረፍተነገር ዉስጥ የድርጊቱን አሉታዊ ጎን ለማቅረብ ፈልገዉ የተጠቀሙት ቃል አፍራሽ በሆነ መልክ ሳይሆን የድርጊቱን ይሁኝታ የሚፈልግ ዓይነት ነዉ። ስለዚህ ‹‹ስኮርጅ የሰዉን እዉቀት ስለምደግፍ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም ››የሚለዉን ‹‹ሲኮርጅ የሰዉን ዕዉቀት ስለሚተማመን ራሱን በራሱ ማስተዳደር አይችልም››በሚለዉ ብገለጽ የተሻለ ነዉ።

#### 4.1.2.3.3 የመስተዋድድ እናየተሳቢ አገባብ ስህተት

በቋንቋ አወቃቀር አብይ የስህተት ምድብ ዉስጥ በስህተት ብዛት መጨሻዉን ደረጃ የያዘዉ የመስተዋድድና የተሳቢ አገባብ ስህተት ነዉ። በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ዉስጥ 17 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል ። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 2.94 %ሲሆን አማካይ ስህተቱ 0.17 ነዉ። የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 0.17 ሆኗል።

በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰት ዉስጥ ከተገኙ የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ ስህተቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ።

ሀ. … ትምህርት የሰዉ ልጅ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ይጠቅማል። /05/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጨ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል።

ለ. … ሰዉ ትምህርት ተምሮ ከተጠናቀቀ በኋላ… /05/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጨ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል።

ሐ. … የኑሮ ዉድነት በሀገራች ( ) ም ሆነ በመንደራች ( ) እጅግ በጣም … /08/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጨ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል።

መ. … እንደ አጋጣሚ በኑሮ ዉድነት ከተመቱ ይህ ( ) ተማር መርዳት አልቻሉም /08/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጩ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ሠ. … የአለማችን ሳይስስትት ያላወቁ ተመርምሮም ያልተደረሰ … /01/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጩ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ረ. … ከዕዉቀት ገበታያቋረጠን ( ) ዮንቨርስት( ) ኮለጅ ( ) በተሀይማኖት ( ) መሸጥ መግዛት ( ) ትራንስፖርት…የገብ ምንጮችን የያዘዉ ቀላል አይምሰላች ኮቪድ19 /01/

ስህተቱ በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የመነጩ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

በምሳሌዎቹ ላይ እንደሚታየዉ ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸዉ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ በመስተዋድድ እና ተሳቢ አጠቃቀም ስህተት ዓረፍተ ነገሮቹ ተድበስብሰዋል።

በምሳሌ 1. ‹‹የ›› አብዛኛዉን ጊዜ ዘርፍ ለማመልከት ስለምትገባ ‹‹ለ››ቢሆን የተሻለ ነዉ።

በምሳሌ 2. ‹‹አጠናቀቀ››በሚለዉ ግስ ላይ ‹‹ከ››መስተዋድድ ለማከል ፈልገዉ ‹‹ከተጠናቀቀ›› ማለታቸዉ በዓረፍተ ነገሩ ዉስጥ ካለዉ አገባብ አንጻር ተገቢነት ስለሌለዉ‹‹ካጠናቀቀ››መባል ነበረበት።

በምሳሌ ሦስት ፣አራት፣ሰባት እና ስምንት ቅንፎቹ በሚያመለክቱት ቦታ ላይ የተሳቢ አመልካች ‹‹ን›› መገደፍ ምክንያት የታዩ ስህተቶች ናቸዉ።

በምሳሌ 5. በ ‹‹በ›› መስተዋድድ ፈንታ ‹‹ተ›› በመጠቀም የተፈጠረ ስህተት ነዉ። በምሳሌ ስድሰት ደግሞ በተከታታይ የሚዘረዘሩ ሀሳቦች ወጥነት ባለዉ መልኩ መቅረብ ስለሚገባቸው በመጀመሪያዉ ቃል ላይ የታከለዉ መስተዋድድ ‹‹ከ›› በተመሳሳይ መልኩ ቀጥሎ ባሉት ሌሎች ቃላት ላይም ከመነሻ መታከል ነበረበት ። ይህም :-

ከዩኒቨርሲቲ፣ከኮሌጅ፣ከበቴሀይማኖት፣ከመሸጥ መግዛት… መባል ነበረበት ።

## 4.2. የስህተት ምንጭ መላምቶች

በስህተት ምንጭ መላምቶች ስር ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ ከተፈጸሙ ስህተቶች በመነሳት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ከሆኑት ዉስጥ በምዕራፍ አንድ በ‹‹ለ›› ስር ለተቀመጠዉ ማለትም ተማሪዎቹ በሚጽፉት ድርሰት ዉስጥ ለስህተቶቹ መከሰት የስህተት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምን ምንድ ናቸዉ ? ለሚለዉ ጥያቄ ለመመለስ ተጥሯል።

የስህተት ምንጮችን በምመለከት በምዕራፍ ሁለት እንደተብራራዉ ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ከተባሉት ዉስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ና በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ዙሪያ የተስተዋሉትን ንዑሳን የስህተት ዝርዝሮችን ለአብነት እየቀረቡ ለማስረዳት ይሞከራል። በተጨማሪም ከስህተት ምንጭ መላምቶች ዉስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀትን በተመለከተ ለመምህራን የጽሁፍ መጠይቆችን የተጠቀመ ሲሆን ለስነልቦናዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ግን መጠይቆችን አልተጠቀመም ።

በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ዉስጥ የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ተብለዉ ከተገመቱት ዉስጥ የሚከተሉት ተብራርተዋል ።

### 4.2.1. የዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

በምዕራፍ ሁለትም እንደተገለጸዉ የዉስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ተማሪዉ ለታላሚዉ ቋንቋ በተወሰነ ደረጃ ከመጋለጡ የተነሳ ያገኛቸዉን ጥቂት ወይም የተወሰኑ የቋንቋዉን ሥርዓቶች በመጠቀም በንግግር ወይም በጽሁፍ ሀሳቡን ለመግለጽ ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ ስህተት ሊፈጽም ይችላል ። እንደዚህ ያሉ ስህተቶች ምንጫቸዉ የታላሚ ቋንቋዎች ዉስብስብ ባህሪይ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ስህተቶች በመሆናቸዉ ስህተቶቹ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት Norrish (1992);Littlewood (1984) ይገልጻሉ። ከቀረቡት የምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለዉ ተማሪዎች በተወሰነ ደረጃ ለታላሚዉ ቋንቋ የምጋለጡ ከሆነ በዚሁ በዉስን የቋንቋዉ ስርዓቶች ሙሉ በሙሉ ከስህተት የፀዳ የታላሚውን ቋንቋ የጽሁፍና የንግግር ህግጋት ሊያስፈጽሙ አይችሉም።

በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ዉስጥ ከተስተዋሉት ስህተቶች ለአብነት ያህል:-

የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ከተብራሩት አስረጅዎች የሚከተሉት ቀርበዋል።

ሀ.በቃላት አመራረጥ ከታዩ ስህተቶች:-

- በተለያዩ ዘናዮችና በተለያዩ ነገሮች እየሰማንና እያየን ነዉ፡፡ /06/
- የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን፡፡ /06/
- የትምህርት ጥቅም ሲባል ደግሞ 1ኛ ገንዘብን ያስገኛል፡፡ /05/

ከቀረቡት ምሳሌዎች መካከል የመጀመሪዉን ብንመለከት ‹‹በተለያዩ ዘናዮችና በተለያዩ ነገሮች እያየንና እየሰማን ነዉ›› የተባለዉ ተማሪዎቹ ስለታላሚዉ ቋንቋ ህግጋት ወይም ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት እና ጥቂቱን የቋንቋዉን ሥርዓት ይዘዉ ሀሳባቸዉን ለመግለጽ ሲሞክሩ የፈጠሩት የቃላት አጠቃቀም ስህተት ይመስላል ። ይህም ‹‹ከመገናኛ ብዙሃን መረጃ እያገኘን ነዉ››ቢባል ከላይ ለማስቀመጥ የፈለጉትን ሀሳብ መግለጽ ይችል ነበር።

የሁለተኛዉን ምሳሌ ብንመለከት ይህም የቃላት ምርጫ ስህተት የተስተዋለበት ነዉ። ‹‹የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን ባሉት ሀሳብ ዉስጥ የቀረቡት ‹‹ቀዉስ ፣ጉዳቱን ›› የሚሉ ቃላት ተቀራራቢ ፍች ሊወክሉ ስለሚችሉ በአንደኛዉ ብቻ ሀሳባቸዉን ቢያቀርቡ የተሻለ ይሆን ነበር።

ይህም ‹‹የኮሮናን በሽታ ጉዳት እንረዳለን ›› ወይም ‹‹የኮሮናን በሽታ ቀዉስ እንረዳለን ›› ቢባል የተሻለ ነዉ።

የሶስተኛዉን ምሳሌ ስንመለከት ‹‹የትምህርት ጥቅም ሲባል ደግሞ 1ኛ ገንዘብን ያስገኛል ›› ይላል ። በዚህ ገለጻ ዉስጥ ‹‹ሲባል ደግሞ ››የሚሉ ቃላት የሚገልጹት ‹‹ሲባል››የሚያመለክተ የሚብራራዉን ጉዳይ ከፊት ለፊት እንደሚያትት የሚጠበቅ ሲሆን ‹‹ደግሞ›› የሚለዉ ቃል ተጨማሪ ነገርን ለማቅረብ የሚያገለግል አያያዥ ነዉ። ስለዚህ ‹‹ሲባል ደግሞ›› ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች ጋር ፍሰቱን ጠብቆ አንድ ላይ መልዕክት ለማቅረብ አብሮ አይሄዱም ።

ለ .በቃላት ድግግሞሽ ስር ከታዩ ስህተቶች :-

አብዛኛዉን ጊዜ ተማሪዎች በጽሁፍ ዉስጥ ለሚፈጥሯቸዉ የቃላት ድግግሞሾች እንደ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉት የታላሚ ቋንቋዎችን ዉስብስብ ባህሪይ በዉል ካለመረዳትም

ሊከሰቱ ስለሚችሉ ስህተቶቹ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት ሊመነጩ ይችላሉ □ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል □

… ስራ ባለመስራታቸዉ ድህነትን በራሳቸዉ ላይ ድህነትን ይጋብዛሉ፡፡ /07/

… ድህነቱ ካልጠፋ ለትዉልድ ስለሚተላለፍ ድህነቱ ለትዉልድ አልፎ ትዉልድ… /07/

… ሰዎች ትምህርት ላይ መቀለድ የለባቸዉም ለምን ከተባሌ የሁሉ በር ከፋች የሆነዉ ትምህርት ነዉ፡፡ /05/

በቃላት ድግግሞሽ ስር የቀረቡትን ምሳሌዎች ብንመለከት ድግግሞሾቹ ታቅደዉና ትኩረት እንድሰጥበት ተፈልጎ የመልዕክቱን ጭብጥ ለማጉላት ተፈልጎ ሳይሆን ስለታላሚዉ ቋንቋ ሥርዓት በቂ ግንዛቤ ካለማስረጽ የመነጩ ይመስላሉ □ ስለዚህ የቃላት ድግግሞሾቹ የዓረፍተ ነገሩን መልዕክት ሰለሚያደበዝዙ በሚከተለዉ መንገድ ቢስተካከሉ የተሻለ ነዉ□

… ባለ መስራታቸዉ ድህነትን በራሳቸዉ ላይ ይጋብዛሉ፡፡ /07/

… ድህነቱ ለትዉልድ አልፎ እንዳይጎዳ … /07/

… ትምህርት ለየትኛዉም ነገር በር ከፋች እንደመሆኑ መጠን ልቀለድ አይገባም፡ /05/

ሐ. በግድፈት ምክንያት ከተስተዋሉ ስህተቶች :-

እንደ Duiay et.al.( 1982,138-139) በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰትቱ ስህተቶች የተለያዩ መግለጫዎች እንዳላቸዉ ገልጸዋል□እነዚህም በምዕራፍ ሁለት የተዘረዘሩ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ግድፈት (ommission) አንደኛዉ ሲሆን በዚህ ዉስጥ ከተስተዋሉት ለአብነት ያህል:-

… በሠላም አስተማር የምሰጠዉን ትም ( ) ርት ተከታተሉ… /04/

… አኖኖርና አመለካከት በጣም የ( ) ሻለ ( ) ዉ፡፡ /05/

… ተማርዉ መርዳ ( ) አ( ) ችሉ /08/

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ዉስጥ መመልከት እንደተቻለዉ በዓረፍተነገር መዋቅር ዉስጥ መገኘት የሚገባቸዉ ተዋቃሪዎች ሳይገኙ በመቅረታቸዉ ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸዉ □ ይኸዉም የቋንቋ ተማሪዉ ታላሚዉን ቋንቋ በከፊል ብቻ ተረድቶ

ሀሳቡን በጽሁፍ ለመግለጽ ሲሞክር የታላሚዉ ቋንቋ ዉስብስብ የመሆኑ ባህሪ ለስህተቱ መፈጠር መነሻ ሊሆን ይችላል።

መ. የቃላት ጭመራ ( እከላ)

ሌላዉ በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት ከሚከሰቱ ስህተቶች መካከል እከላ ( simple addition) የሚጠቀስ ሲሆን በዚህ ምክንያት በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ዉስጥ ከተስተዋሉት ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል።

… አንድ ተማሪ ትህምህርቱን መማር ስጀምር … /08/

… ይህ ኮሮና በሽታ በህብረተሰቡ ላይ አስግ ችግር እያደረሰ መሆኑ …

… በዚሁ የኮሮና በሽታ ቀዉስ ጉዳቱን እንረዳለን ።

ከቀረቡት አስረጅዎች መረዳት እንደሚቻለዉ በዓረፍተ ነገሮቹ ዉስጥ የተሰመረባቸዉ ድምጾችና ቃላት ለቦታዉ ሳያስፈልጉ የታከሉ ናቸዉ።

የቋንቋ አወቃቀርን በተመለከተ

ሀ.የአረፍተ ነገር ስሙምነት አለመኖር

1. ተማሪዎችም ሠላም አገኝቶ ትምህርትን ተማሩ

2. መፍትሄዉ ጠንክሮ መስራትና ደህነትን ማጥፋት

3. ሰዎች ትምህርት ላይ መቀለድ የለባችሁም።

4. ያልተማረና የተማረ ሰዎች መድረክ ላይ አወተን ብናወዳድ

ከቀረቡት ምሳሌዎች መካከል የመጀመሪያዉን ዓረፍተ ነገር ብንመለከት የቁጥር እና የመደብ አጠቃቀም ስህተት ይታይበታል። ይህም‹‹ ተማሪዎችም ››የሚለዉ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት በ3ኛ መደብ ÷ብዙ ቁጥር ተገልጾ የዓረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ ደግሞ በ3ኛ መደብ ÷ብዙ ቁጥር የቀረበ ነዉ።ስለዚህ በዓረፍተ ነገሩ ተሳቢ ጓዝ ላይ ‹‹አገኝቶ››በማለት የቀረበዉ 3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ነዉ፡፡ ‹‹አግኝተዉ›› በሚል ማስተካከሉ ዓረፍተነገሩን ከቁጥር እና መደብ ስህተት ያርመዋል ።ይህም ‹‹ተማሪዎቹም ሰላም አግኝተዉ ትምህርትን ይማራሉ ወይም ተማሩ›› ቢባል የተሻለ ነዉ ።

በምሳሌ ሁለት ላይ የቀረበዉ ዓረፍተ ነገር የሚታይበት ስህተት ÷ዓረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀጽን ያለ መያዙ ነዉ □

ይህም ዓረፍተ ነገሩ ‹‹ መፍትሄዉ ጠንክሮ መስራትና ደህነትን ማጥፋት ( )›› በሚለዉ ቦታ ‹‹ ነዉ›› የሚል ግስ ቢታከልበት የተሻለ ይሆናል□

በምሳሌ ሦስት ላይ የቀረበዉ ዓረፍተ ነገር የሚታይበት ስህተት የመደብ ነዉ□ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት በ3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተገለጸ ሲሆን የዓረፍተ ነገሩ ግስ ደግሞ በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተቋጨ ነዉ □ ስለዚህ የመደብ ስህተቱ ማሰሪያ አንቀጹን በሦስተኛ÷ብዙ ቁጥር ‹‹የለባቸዉም›› ቢቋጭ ዓረፍተ ነገሩ ከመደብ ስህተት የታረመ ይሆናል □

በምሳሌ አራት የቀረበዉ ዓረፍተ ነገር የሚስተዋልበት ስህተት የቁጥር አለመስማማት ነዉ□ ይኸዉም የዓረፍተ ነገሩ ባለበት ‹‹ሰዎች›› በብዙ ቁጥር የተገለጸ ሲሆን የስም ገላጮቹ ግን በነጠላ ቁጥር ‹‹ ያልተማረናየተማረ›› በሚል የቀረቡ ናቸዉ፤ ስለዚህ ‹‹ያልተማሩናየተማሩ›› በማለት ቢናስተካክል የተሻለ ይሆናል

በአጠቃላይ ከላይ የተቀመጡት ስህተቶች በዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት በቋንቋ አወቃቀር ስር የታዩ ስህተቶች ናቸዉ □

ለ.የመስተዋድድና የተሳቢ አገባብ

… ከዕዉቀት ገበታ ያቋረጠን ዩንቨርስት ኮለጅ በተሀይማኖት መሸጥመግዛትን ትራንስፖርት የገብምንጮችን የያዘዉ ቀላል አይምሰላች ኮቪድ 19

… ከደረሰ በኃላም እራሱ ይለዉጣል ፣በተሰቦቹንም ይለዉጣል□

በምሳሌ አንድ የቀረበዉ የዓረፍተ ነገር ስህተት በመጀመሪያዉ ቃል ላይ የታከለዉ መስተዋድድ ‹‹ከ ›› ወጥነት ባለዉ መልኩ በተከታታይ በተዘረዘሩት ቃላት ላይ አልታከለም ፤ስለዚህ በዚህ መልኩ ‹‹ ከዩኒቨርሲቲ፣ከኮለጅ፣ከቤቱሀይማኖት፣ከመሸጥመግዛት ፣ከትራንስፖርት እና ከገቢ ምንጮች የያዘዉ ቀላል አይምሰላችሁ ኮቪድ 19! ቢባል የተሻለ ይሆናል □

በምሳሌ ሁለት በተከታታይ በቀረቡ ሁለት ሀሳቦች ስር ከተደጋገሙ ግሶች ዉስጥ አንደኛዉን ‹‹ይለዉጣል›› በማስቀረት ‹‹ እራሱ ›› በሚለዉ ላይ የተሳቢ አመልካች / ን / በመጨመር ሁለቱን ሀሳቦች በአያያዥ ‹‹እና›› በማጣመር ስህተቶቹን ማረም ይቻላል ።

… ከደረሰ በኃላ እራሱን እና ቤተሰቦቹን ይለዉጣል ።

በአጠቃላይ ከላይ በመስተዋድድ እና በተሳቢ አገባብ ምክንያት ስህተቶች የተስተዋሉባቸዉ ዓረፍተ ነገሮች በዉስጠ ቋንቋ ህግጋትና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ካለማግኘት ሀሳብን አስፋፍቶ ለመግለጽ ሲሞከር የሚመነጩ ስህተቶች ናቸዉ ብሎ መገመት ይቻላል ።

### 4.2.2.የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አዲስ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ስናደርግ የቀደመዉ ቋንቋ ጣልቃ የሚገባበት ሂደት ነዉ።ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የተወሰነ ክፍተት ሲያጋጥማቸዉ ያን ክፍተት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉን ተጠቅመዉ ለመሙላት ይፈልጋሉ ።

ስለዝህ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የታላሚዉን ቋንቋ ቅርጽ ከአፍ መፍቻ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁነታ ወይም ተቀራራቢነት ባለዉ መንገድ ያመነጫል ። ይህም በተማሪዉ ንግግርም ሆነ ጽህፈት ዉስጥ የሚታዩ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዉ የድምጽ ፣የቃላት አጠቃቀም ፣የሀረግና የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ዉስጥ ሊስተዋል የሚችል ቢሆንም ስህተቱ ጎልቶ የሚታየዉ ግን በንበት በመሆኑ ከንግግር ቅላጼ ( ቃና) በመነሳት የተናጋሪዉን ማንነት ማወቅ እንደሚቻል edge (1989፣7-9) ያብራራል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ ከተስተዋሉት ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ መነሻነት ነዉ ሲባል እንደ ‹‹ Ambassadder Neechreraasha Apari Bacuri (2000 ) በተደረገዉ Shekigna Amharic English Shekigna dictionary መረጃ (ጥናት) መሰረት የሸክኛ ቋንቋ ሃያ ሰባት ድምጾች መካከል አምስቱ ቋሚ አናባቢዎች የሚባሉት 1.a አ 2.e ኤ 3.iኢ 4. Oኦ 5. U ኡ ናቸዉ ። በአማርኛ ግን ሰባት አናባቢዎች ሲገኙ ከእነዚህ ዉስጥ ግን / ኧ / ና/ እ/ በሸክኛ ቋንቋ ዉስጥ የሉም ።

በሸክኛ ቋንቋ ግንደ ቃል ወይም ስርወ ቃል መመስረት የማይችሉ ስድስት ተነባቢያን l፣ j ፣p፣s፣ r፣ ch፣ አስራ ስድስት ተነባቢያን እና በአምስት አናባቢያን የሚጠሩ ቃላት አጨራረሳቸዉ በአብዛኛዉ በ ‹‹ 0ኦ ›› ድምጽ ነዉ ።

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸዉ ድርሰቶች ዉስጥ በርካታ የአናባቢ ድምጸ ልሳናት አጠቃቀም ስህተቶች ተስተዉለዋል ፡ ለአብነት የሚከተሉት ቀርበዋል።

በሽክኛ ቋንቋ በአናባቢ /ኧ / ና /እ /አለመኖር ምክንያት በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ዉስጥ ከተስተዋሉ ስህተቶች የሚከተሉት ለአብነት ቀርቧል።

ሀ… አስፈርና አስግ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንሜለከታለን…

ለ… አንድ ተማር ትህምህርቱን መማር ስጀምር…

ሐ… ካጋሜሰ በኃላ አጋጣም …

መ… ዮንፎርሙ ተቀደዉ የሚያሰፋበትና …

ሠ… ስራ ሰርቶ ለመኖር በጣም አሰልች በመሆኑ…

ረ…አስተማርያች ሰላም አገኝቶ ተማሪዎችሁን…

ሰ… ኩረጃ በተመለከቴ ራሱየሚኮርጂን ተማምኖ አይኖርም …

ሸ… ኩረጃን ከትምህርትበት እናስወግድ …

ቀ… ተማርም ሰላም አቶ አስተማርም ሰላም አቶ በተጨነቀ …

ከላይ በአረፍተ ነገሮች ዉስጥ የተሰመረባቸዉ ቃላት መጻፍ ወደ ነበረባቸዉ ቢስተካከሉ የሚያመለክቱትን ለዉጥ ተጠኚዎቹ ከፃፉት ጋር እያስተያዩ መመልከት ይቻላል

**ሠንጠረዥ 6. አናባቢ / ኧ/ ና / እ / በሸክኛ ቋንቋ ዉስጥ ባለመኖራቸዉ በተጠኚ ተማሪዎቹ የቃላት አጻጻፍ ላይ የተስተዋሉ ስህተቶች**

| ተ.ቁ | ስህተት ያለበት ቃል | ለመጻፍ የተፈለገዉ ቃል | የአናባቢዎች ለዉጥ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | አስፈር | አስፈሪ | እ ----- ኢ |
| | አስግ | አስጊ | እ------ ኢ |
| | እንሜለከታለን | እንመለከታለን | ኤ------ኧ |
| ለ. | ተማር | ተማሪ | እ------ኢ |
| | ስጀምር | ሲጀምር | እ------ ኢ |
| ሐ. | ካጋሜሰ | ካጋመሰ | ኤ------ ኧ |
| | አጋጣም | አጋጣሚ | እ------- ኢ |
| መ. | ዮንፎርሙ<br>የምያሰፋበት | ዩኒፎርሙ<br>የሚያሰፋበት | ኦ-------ኡ -<br>እ---------ኢ |
| ሠ. | አሰልች | አስልቺ | እ--------ኢ |
| ረ. | አስተማር<br>አገኝቶ | አስተማሪ<br>አግኝተዉ | እ-------- ኢ<br>ኦ--------ኧ |
| ሰ. | ኩርኛ<br>በተመለከቴ<br>የምኮርጂ | ኩረኛ<br>በተመለከተ<br>የሚኮርጅ | እ---------ኧ<br>ኤ-----ኧ<br>ኢ------እ |
| ሸ. | ኩርኛ | ኩረኛ | እ-------ኧ |
| ቀ. | ተማርም አጥቶ<br>አስተማርም | ተማሪም<br>አጥተዉ<br>አስተማሪም | እ--------ኢ<br>ኦ------ኧ<br>እ------ኢ |

ባጠቃላይ ከላይ በማብራሪያዉ እና በሰንጠረዥ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቃላት ውስጥ የሚታዩት ድምፆች መፃፍ በነበረባቸው ሣይሆን በተለያዩ የፊደል ዝሪያዎች ተተክተው ቀርበዋል፡፡ ለምሣሌ ግዕዝ ፊደል በሀምስ ‹‹እን<u>መ</u>ለከታለን›› ን‹‹እን<u>ሜ</u>ለከታለን›› ፣ሳልስ ፊደልን በሳድስ ‹‹ አስፈ<u>ሪ</u> ›› ን ‹‹አስፈ<u>ር</u>›› እና አንዳንድ ግሶች በ ‹‹0 ኦ ›› የመጨረስ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ‹‹ አጥቶ ›› የምሉትና ሌሎች ከላይ የቀረቡት ልዩነቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ አመለካቾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### 4.2.3.የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸዉ ምክንያቶች መካከል የማስተማሪያ መሳሪያዎች (መርሃ ትምህርቱ፣መማሪያ መፃህፍት፣አጋዥመፃህፍት፣) እና መምህራን የሚከተሏቸዉ የማስተማሪያ ዘዴዎች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ በስህተት ትንተና ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን እንዳብራሩ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡Broughton (1978፡134) በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ስህተት እንድከሰት ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉት ነገሮች ዉስጥ መርሃ ትምህርቱ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣መምህራንና ተማሪዎች እንደሚጠቀሱ ይገልፃሉ፡፡በዚህ ጥናትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ስህተት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለዉ በተለያዩ ምሑራን የቀረቡ ሀሳቦችን መሰረት ባደረገ መልኩ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅሁፍ መጠይቆች (Questionnaries) ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7. የመማር ማስተማር ሂደትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀትን በተመለከተ ከተማሪዎች የቀረቡ ምላሾች

| ተ.ቁ | | በጣም | ከፍተኛ | ከፍ | ተኛ | መካ | ከለኛ | ዝ | ቅተኛ | በጣም | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ መፅሀፉ ለድርሰት ፅሀፈት ክንዉን ትኩረት ስለመስጠቱ | 3 | 7.5 | 5 | 12.5 | 7 | 17.5 | 23 | 57.5 | 2 | 5 |
| 2. | መምህራን በክፍልና በተለያዩ አጋጣሚዎች ፅሀፈትን የማለማመዱ ሂደት | 2 | 5 | 4 | 10 | 9 | 22.5 | 21 | 52.5 | 4 | 10 |
| 3. | መምህራን የአማርኛን ትምህርት ዉብ፣ማራኪ፣ናአሳታፊ አድርጎ የማቅረባቸዉ ስልት | 11 | 27.5 | 6 | 15 | 14 | 35 | 8 | 20 | 1 | 2.5 |
| 4. | መምህራንስለ ድምፆች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዐረፍተነገሮች አቀነጃጀት ትኩረት ሰጥተዉ ማፃፍ | 7 | 17.5 | 11 | 27.5 | 18 | 45 | 3 | 7.5 | 2 | 5 |
| 5. | መምህራን ፅሀፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ብቻ የተገደቡ ይመስላሉ | 28 | 70 | 5 | 12.5 | 1 | 2.5 | 5 | 12.5 | 1 | 2.5 |
| 6. | መምህራን ከመማሪያ መፅሀፉ ይዘቶች በተጨማሪ ከመፅሄቶች ከመፃህፍት ከተሌቪዥንና ሬዲዮ መረጃ ሰብስባችሁ በፅሁፍ እንድታቀርቡ ማድረጋቸዉ ሂደት | 2 | 5 | 1 | 2.5 | 6 | 15 | 29 | 72.5 | 2 | 5 |
| 7. | መምህራችሁ የሚመቻችሁን ርዕሶች መርጣችሁ ድርሰት እንድትፅፉ የመከታተሉ ሂደት | 6 | 15 | 4 | 10 | 9 | 22.5 | 17 | 42.5 | 4 | 10 |
| 8. | የመምህራን የመልመጃ አስተራረም ይዘት በድምፆች፣በቃላት፣በመልዕክት ቅደም ተከተላዊ አቀነጃጀት፣በቃላት ግልፀትና ሀሳብ ጥንካሬ ላይ ትኩረት ስለመስጠቱ በተመለከተ | 3 | 7.5 | 6 | 15 | 15 | 37.5 | 11 | 27.5 | 5 | 12 |
| 9. | አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለህ ያለህ /ሽ ፍላጎት | 9 | 22.5 | 8 | 20 | 12 | 30 | 7 | 17.5 | 4 | 10 |
| | የአፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ልብህ/ሽ እንድትጠቀም/ሚ ያሳደረዉ ተፅዕኖ | 10 | 25 | 7 | 17.5 | 15 | 37.5 | 5 | 12.5 | 3 | 7.5 |

በሠንጠረዥ ሰባት ላይ በቀረበዉ መረጃ መሰረት መጠይቁን የሞሉት 40 ተማሪዎች ዉስጥ ለመጀመሪያዉ ጥያቄ ‹‹የመማሪያ መፅሀፉ ለድርሰት ፅህፈት ክንዉን ምንያህል ትኩረት ሰጥቷል? ››የሚለዉ ሲሆን ጥያቄዉን ከመለሱ 40 ተማሪዎች ዉስጥ 3 ተማሪዎች (7.5%) በጣም ከፍተኛ፣5 ተማሪዎች (12.5%) ከፍተኛ፣ 7 ተማሪዎች (17.5%) መካከለኛ፣23 ተማሪዎች (57.5%) ዝቅተኛ እንዲሁም 2 ተማሪዎች (5%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ በዚህም መሰረት የመማሪያ መፅሀፉ ለድርሰት ፅህፈት ክንዉን ትኩረት ያለመስጠቱን 25 ተማሪዎች (62.5%) የሚሆኑት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡ለመምህራን የቀረበዉ የመጀመሪያዉ ቃለመጠይቅ ‹‹የመማሪያ መፅሀፉ ለጽህፈት ክሂል ምን ያህል ትኩረት ይሰጣል?›› የሚል ነበር፡፡ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘዉ መረጃም የመማሪያ መፅሀፉ ለፅህፈት ክሂል እንደሌሎቹ የዕዉቀት ዘርፎች ትኩረት ሰጥቶ እንደማያሰራና በዝቅተኛ ደረጃ ፅህፈትን የማለማመድ ሚና እንደሚወጣ ገልፀዋል፡፡

ሁለተኛዉ ጥያቄ ‹‹መምህራን ተማሪዎቻቸዉን በክፍልና በቤት ፅህፈትን የማለማመዱ ሂደት ምን ይመስላል?›› የሚለዉ ሲሆን ለጥያቄዉ የሰጡት መልስም በጣም ከፍተኛ 2 ተማሪዎች (5%)፣ከፍተኛ 4 ተማሪዎች (10%)፣መካከለኛ 9 ተማሪዎች (22.5%)፣ዝቅተኛ 21 ተማሪዎች (52.5%) እና ዝቅተኛ 4 ተማሪዎች (10%) በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተዉ ተማሪዎችን በክፍልና ከክፍል ዉጭ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ፅህፈትን የማለማመዱ ሂደት ዝቅተኛ (52.5%) መሆኑን ያስረዳል፡፡ ለመምህራን የቀረበዉ ቃለ መጠይቅም ‹‹ተማሪዎችዎን በተለያዩ አጋጣሚዎች ፅህፈትን በምን መልኩ ያለማምዷቸዋል?›› ለሚለዉ በመማሪያ መጽሀፉ የቀረበዉን የማለማመድ ሂደት የተጠበቀ ሆኖ ከዚያ ያለፈ በሰፊዉ ለማለማመድ ያላቸዉ ክፍለ ጊዜ ጭምር ዉስን እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡

ሦስተኛዉ ጥያቄ ‹‹መምህራን የአማርኛን ትምህርት ዉብ፣ማራኪና አሳታፊ አድርጎ የማቅረባቸዉ ስልት ምን ይመስላል?›› የሚለዉ ሲሆን የሰጡት ምላሽም 11 ተማሪዎች (27.5%) በጣም ከፍተኛ፣6 ተማሪዎች (15%) ከፍተኛ፣መካከለኛ 14 ተማሪዎች (35%)፣ዝቅተኛ 8 ተማሪዎች (20%)፣በጣም ዝቅተኛ 1 ተማሪ (2.5%) በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያስረዳዉ የአማርኛን ትምህርት ዉብ፣ማራኪና አሳታፊ አድርገዉ የማቅረባቸዉ ሂደት መልካም እንደሆነ ያስረዳል፡፡ መምህራን ‹‹የአማርኛን ትምህርት አሳታፊ፣ዉብና ማራኪ አድርጎ የማቅረብ ስልት ለመምህሩ ሙያዊ ግዴታዉ እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የትምህርቱን ይዘት አሳታፊ፣ዉብና ማራኪ አድርገዉ

መምህራን ስለማቅረባቸዉ 27.5% በጣም ከፍተኛ፣15%ከፍተኛ እና 35% መካከለኛ በማለት የአቀራረብ ስልቱን ማራኪነት ተማሪዎችም አስቀምጠዋል፡፡

‹‹መምህራን ስለ ድምፆች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዐረፍተ ነገሮች አቀነጻጀት በተመለከተ ትኩረት ሰጥተዉ የማፃፋቸዉ ሂደት በምን መልኩ ነዉ?›› ለሚለዉ 7 ተማሪዎች (17.5%) በጣም ከፍተኛ፣11 ተማሪዎች (27.5%) ከፍተኛ፣18 ተማሪዎች (45%) መካከለኛ፣3 ተማሪዎች (7.5%) ዝቅተኛ እና 2 ተማሪዎች (5%)በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ መምህራንም ለቀረበላቸዉ ጥያቄ ‹‹ስለ ድምፆች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዐረፍተ ነገሮች አቀነጻጀት ትኩረት ሰጥተዉ ያፅፏቸዋል?››ለሚለዉ መምህራኑ በመፅሀፉ ዉስጥ በቀረቡት ይዘቶች ስር በተዘዋዋሪ ስለሚሰጡ እንደየ አቀራረባቸዉ እየፃፉ ያሉበትን ሁኔታ አስቀምጠዋል፡፡ስለዚህ ስለ ድምፆች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዐረፍተ ነገሮች አቀነጻጀት በጣም ከፍተኛ ትኩረት ባይሰጡም እንደ አቀራረብ ስልቱ ያፅፏቸዋል ማለት ነዉ፡፡

‹‹መምህራን ፅህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መፅሀፉ ብቻ የተገደቡ ይመስላሉ?››ለሚለዉ 28 ተማሪዎች (70%) በጣም ከፍተኛ፣5 ተማሪዎች (12.5%) ከፍተኛ፣1 ተማሪ (2.5%) መካከለኛ፣5 ተማሪዎች (12.5%) ዝቅተኛ እና 1 ተማሪ (2.5%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመምህራን የቀረበዉ ቃለ መጠይቅ ‹‹ፅህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መፅሀፉ የተገደበ ነዉ? ወይስ ምን ዓይነት አማራጮች ይጠቀማሉ?›› ለሚለዉ መምህራኑ ፅህፈት ክሂልን ለማለማመድም ሆነ ሌሎቹን ክሂሎች ለማስተማር በዋነኝነት የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ የተገደበ እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡በተመሳሳይ መልኩ 85% የተማሪዎች ምላሽም ፅህፈትን ለማስተማር መምህራን የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ የተገደበ መሆኑን ነዉ፡፡ይህ የሚያመለክተዉ መምህራን ተማሪዎቻቸዉን ፅህፈት ለማለማመድ በመማሪያ መፅሀፉ ከመወሰን ዉጭ ከዚያ ባሻገር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ፅህፈትን የማለማመዱ ሂደት ብዙም ትኩረት እንዳልተሰጠበት ነዉ፡፡

‹‹መምህራን ከመማሪያ መፅሀፉ ይዘቶች በተጨማሪ ከመፅሄቶች ፣ ከጋዜጦች ፣ ከመፃህፍት ፣ከቴሌቪዥንና ሬዲዮ መረጃ በሰብስባችሁ በፅሁፍ እንድታቀርቡ የማድረጋቸዉ ሂደት ምን ይመስላል?›› ለሚለዉ 2 ተማሪዎች (5%) በጣም ከፍተኛ፣1 ተማሪ (2.5%) ከፍተኛ፣6 ተማሪዎች (15%) መካከለኛ፣29 ተማሪዎች (72.5%) ዝቅተኛ እና 2 ተማሪዎች (5%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተዉ መምህራን የማስተማር

ስልታቸዉ ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መፅሀፉ የተገደበ መሆኑን ካስቀመጡት ሀሳብ ጋር የሚገናኝ ነዉ፡፡77.5% ተማሪዎች ከመገናኛ ብዙሀን መረጃ ሰብስበዉ በፅሁፍ እንድያቀርቡ የማለማመዱ ሂደት እንደማይተገበር ምላሽ የሰጡትም ከዚሁ ጋር ይያያዛል፡፡

‹‹መምህራን የሚመቻችሁን ርዕሶች መርጣችሁ ድርሰት እንድትፅፉ የመከታተል ሂደታቸዉ ምን ይመስላል?›› ለሚለዉ 6 ተማሪዎች (15%) በጣም ከፍተኛ፣4 ተማሪዎች (10%) ከፍተኛ፣9 ተማሪዎች (22.5%) መካከለኛ፣17 ተማሪዎች (42.5%) ዝቅተኛ እና 4 ተማሪዎች (10%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መረጃ ሰጥተዋል፡፡ይህ የሚያመለክተዉ ተማሪዎች በፈለጉት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ፅሁፈትን እንድለማመዱ እድል እንደማይሰጣቸዉ ያመለክታል፡፡

‹‹የመምህራን የመልመጃ አስተራረም ይዘት ትኩረት በድምፆች፣በቃላት፣በሀረጋት፣በዐረፍተ ነገሮች አቀነጃጀት፣በመልዕክት ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀት፣በቃላት ግልፀት እና በሀሳብ ጥንካሬ ላይ ትኩረት ይሰጣል?›› ለሚለዉ 3 ተማሪዎች (7.5%) በጣም ከፍተኛ፣6 ተማሪዎች (15%) ከፍተኛ፣15 ተማሪዎች (37.5%) መካከለኛ፣11 ተማሪዎች (27.5%) ዝቅተኛ እና 5 ተማሪዎች (12.5%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ‹‹የመልመጃ አስተራረም ይዘትዎ በድምፆች፣ በቃላት፣በሀረጋት፣በዐረፍተ ነገሮች አቀነጃጀት፣በቃላት ግልፀት፣በሀሳብ ጥንካሬና የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ወዘተ ላይ ምን ያህል ትኩረት ያደርጋሉ?›› ለሚለዉ መምህራኑ ለእነዚህ ለእያንዳንዱ ተናጠላዊ ትኩረት ባይሰጥም በዐረፍተ ነገር ሥርዓትና እንደ መልመጃዎቹ ትዕዛዝ የአስተራረም ሂደቱ እንደሚከናወን ገልፀዋል፡፡ይህ የሚያመለክተዉ የመልመጃ አስተራረም ስልቱ እያንዳንዱን አብጠርጥሮ የሚመለከት ሳይሆን እንደ መፅሀፉ የመልመጃ አቀራረብና ትዕዛዝ የሚወሰን መሆኑን ነዉ፡፡

‹‹ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸዉ ፍላጎት ምን ይመስላል?›› ለሚለዉ 9 ተማሪዎች (22.5%) በጣም ከፍተኛ፣8 ተማሪዎች (20%) ከፍተኛ፣12 ተማሪዎች (30%) መካከለኛ፣7 ተማሪዎች (17.5%) ዝቅተኛ እና 4 ተማሪዎች (10%) በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ይህ የሚያመለክተዉ ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን ለመማር አዎንታዊ አመለካከት እንጂ አሉታዊ እንደማያንፀባርቁ ያስገነዝባል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመምህራን በቀረበዉ ቃለ መጠይቅ ‹‹ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸዉ ፍላጎት በትምህርቱ ሂደት በምን መልኩ ይንፀባረቃል?›› ለሚለዉ መምህራኑ ተማሪዎቹ አማርኛን ለመማር ጥሩ ፍላጎት ያላቸዉ እንደሆነና ምንም ዓይነት የተቀዛቀዘ ስሜት እንደማያሳዩ ገልፀዋል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ልብ እንዳይጠቀሙ የሚያደርገዉን ተጽዕኖን በተመለከተ 10 ተማሪዎች (25%) በጣም ከፍተኛ፣7 ተማሪዎች (17.5%) ከፍተኛ፣15 ተማሪዎች (37.5%) መካከለኛ፣5 ተማሪዎች (12.5%) ዝቅተኛ እና 3 ተማሪዎች (7.5%) በጣም ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይህ የሚያመለክተዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ አማርኛ ቋንቋን በመማሩ ሂደት ተፅዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ይኸዉም የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛን ቋንቋን በመማር ሂደት የሚያሳድረዉ ተፅዕኖ ዝቅተኛ ነዉ፡፡ያሉት ተማሪዎች 20% ሲሆኑ ቀሪዎቹ 80% ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ እስከ መካከለኛ ባሉ አማራጮች ስር ምላሽ የሰጡ ናቸዉ፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመምህራን በቀረበላቸዉ ቃለመጠይቅ ‹‹የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ልብ እንዳይጠቀሙ ያሳደረዉ ተፅዕኖ ይኖራል?በምንስ ይገለፃል?››ለሚለዉ መምህራኑ የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን በንግግርና በፅሁፍ የሚያሳዩ ቢሆንም በአብዛኛዉ ግን በፅህፈት ላይ የሚስተዋል እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡ይኸዉም በፅህፈት ሂደት በድምፆች የአጠቃቀም ሂደት ላይ በሰፊዉ እየታዩ ያሉ ክፍተቶች እንዳሉ አስቀምጠዋል፡፡

ከላይ የቀረበዉ መረጃ እንደሚያመለክተዉ የመምህራን የመልመጃ አስተራረም ስልት (የድርሰት እርማት ዘዴ) ተገቢዉን ሂደት ጠብቆና አብጠርጥሮ የሚመለከት ያለመሆኑን ያሳያል፡፡

ባጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የማስተማሪያ መሳሪዎች አዘገጃጀት ክፍተት በታላሚዉ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን ለስህተት ከሚያጋልጧቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ እንደሚካተቱ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች ያስገነዝባሉ፡፡ስለሆነም የተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ለስነልሳን የዕዉቀት ዘርፎች እኩልትኩረት ያለመስጠት ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂል ላይ በቂ ልምምድ እንዳያደርጉ፣መምህራን በመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ ተመርኩዘዉ ለጽህፈት በቂ ጊዜ ያለመስጠታቸዉ፣ በጣም አልፎ አልፎ የሚካሄደዉ የመምህራን የድርሰት አሰተራረም እራሱ በዓረፍተ ነገር ሥርዓት ላይ ብቻ መመርኮዙ ተማሪዎች በድርሰት ጽህፈቶቻቸዉ ዉስጥ ለሚያሳዩት ስህተቶች የስህተት ምንጮች እንደሆኑ ተገምቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መለየትና ለስህተቶቹ መፈፀም ምክንያት የሆኑ ምንጮችን መጠቆምና ማብራራት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በጥናቱ ሊመለሱ የምገባቸው ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ተጠቅሰዋል፡፡

እነሱም፡-

1. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶች ምን ምንድ ናቸው?

2. ለእነዚህ ስህተቶች መከሰት የስህተት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምን ምንድ ናቸው?

ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎች ከተፃፉ ድርሰቶች፣ ከመምህራንና ተማሪዎች  የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን በሚከተሉት ግኝቶች ላይ ተደርሷል፡፡

ሀ.በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች፡-

በጥናቱ ዉጠትመሰረት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ከሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች ተማሪዎቹ ሁለት ጊዜ በጻፏቸዉ 64 ድርሰቶች ዉስጥ 1498 ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ የስህተቶቹ አማካይ ስርጭት ሲሰላ 23.40 ሲሆን በመቶ ቃላት ዉስጥ የሚገኘዉ የስህተት ድግግሞሽ 5.47 % ይሆናል፡፡

በዚህ ጥናት ዉስጥ ጎልተዉ የታዩት የስህተት ዓይነቶች በሦስት ምድብ ተቀምጠዋል ፡፡

እነርሱም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት እና የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ናቸዉ፡፡

ከሦስቱ የስህተት ምድቦች ከፍተኛዉን ቁጥር የያዘዉ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን 941 (62.54%) ያህል ሆኗል። ይህ የስህተት ምድብ የቃላት አመራረጥ ፣የቃላት ድግግሞሽ፣ የቃላት ጭመራ (እከላ) ፣የሆሄያት ግድፈት እና ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ያለመጠቀም ስህተቶችን በስሩ አካቷል።

በድርሰቶቹ ዉስጥ ከተገኙ አጠቃላይ ስህተቶች መካከል ሁለተኛዉን ደረጃ የያዘዉ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን 353 (23.36%) የስህተት መጠን ይዟል።

ይህ የስህተት ምድብ የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ፣የድርብሠረዝ አጠቃቀም ስህተት፣የነጠላሠረዝ አጠቃቀም ስህተት፣የትዕምርተ አንክሮ (ቃለ አጋኖ) አጠቃቀም ስህተት ፣የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት እና የሁለት ነጥብ ከሠረዝ አጠቃቀም ስህተት የተከሰቱ ስህተቶችን ይዟል።

ከሦስቱ የመጨረሻዉን ቁጥር የያዘዉ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነዉ። የስህተት ምድቡ በአጠቃላይ ድርሰቶች ዉስጥ ከተገኙት 174 (11.28%) ያህሉን ይዟል። በዚህ የስህተት ምድብ ዉስጥ የተካተቱት የዐረፍተ ነገር ስሙምነት ያለመኖር ፣የቃላት አጠቃቀም ፣የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ ናቸዉ።

በዚህ ጥናት ዓላማ መሰረት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች የስህተት ምንጭ ይሆናሉ የተባሉ ምክንያቶችን ለመጠቆም ተሞክሯል።

ለ. ዋና ዋና የስህተት ምንጮች

በተማሪዎቹ ከተጻፉ ድርሰቶች መረጃዎችን በማገናዘብ የተገኙ ስህተቶችን ከሁለት ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ጋር ለማገናኘት ተሞክሯል። እነርሱም የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ናቸዉ።

- <u>የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ</u> :- የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ተማሪዉ ለታላሚዉ ቋንቋ በተወሰነ ደረጃ ከመጋለጡ የተነሳ ስለ ታላሚዉ ቋንቋ ህግጋት እና ሥርዓት በቂ የሆነ ግንዛቤ ባለማግኘታቸዉ የሚያዉቋቸዉን ጥቂት የቋንቋዉን ሥርዓቶች ይዘዉ ሀሳባቸዉን ለመግለጽ ሲሞክሩ በታላሚዉ ቋንቋ ዉስብስብ ባህሪ ምክንያት ለተለያዩ ስህተቶች እንደተዳረጉ ተገምቷል። ስህተቶቹም የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ :- የቃላት አመራረጠጥ፣ የቃላት ድግግሞሽ፣ግድፈት፣ የቃላት እከላ(ጭመራ) እና

ሆሄያትን በተገቢ ቅርጻቸዉ ያለመጠቀም ሲሆኑ የቋንቋ አወቃቀርን በተመለከተ :- የዓረፍተ ነገር ስሙምነት ያለመኖር ፣ የመስተዋድድ እና የተሳቢ አገባብ ስህተቶች ናቸዉ፡፡

- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ :- ተማሪዎች አዲስ ቋንቋን ለመልመድ ጥረት ሲያደርጉ የቀደመዉ ቋንቋ ጣልቃ እየገባ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያዳብር እንደቻለ ተገምቷል።ይህም ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የተወሰነ ክፍተት ሲያጋጥማቸዉ ያን ክፍተት የአፍመፍቻ ቋንቋቸዉን ተጠቅመዉ ለመሙላት ሲፈልጉ የተከሰቱ ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በዚህም መሰረት ከተከሰቱት ስህተቶች መካከል በዋነኝነት ተጠቃሽ የሚሆነዉ የአናባቢ ድምጸ ልሳናት አጠቃቀም ስልት ነዉ፡፡ይሄዉም በሽክኛ ቋንቋ ዉስጥ /ኧ/ ና /ኢ/ አናባቢዎች ባለመኖራቸዉ ምክንያት /ኢ/ በ /እ/ ፣ /ኧ/ በ /ኤ/ ለዉጦ መጻፍ እና ሌላዉ በሽክኛ ቋንቋ በሚገኙ በሃያ ሁለቱ ተናባቢያንና በአምስቱ አናባቢያን የሚጠሩ ሃያ ሰባቱም ድምጾች የቃላት አጨራረሳቸዉ በአብዛኛዉ በ ‹‹ 0ኦ›› ድምጽ ነዉ። ስለዚህ ተማሪዎቹ /ኧ/ በ /ኦ/ ፣ /ኡ / በ /ኦ / ተጠቅመዉ አንዳንድ ቃላትን በግሶቻቸዉ ላይ ሲቋጩ ወይም ሲያስሩ የተስተዋለዉ ተግባር በዚሁ ምክንያት ሊሆን እንደቻለ ይገመታል።

- የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለስህተት ከሚያጋልጧቸዉ ምክንያቶች ሌላዉ ተጠቃሽ ታላሚዉን ቋንቋ የማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ክፍተት ነዉ፡፡ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከቀረበዉ የቃለ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች እንዳመለከቱት ተማሪዎችን ለድርሰት ጽህፈት ስህተት ከዳረጉዋቸዉ ምክንያቶች ሌላዉ ተጠቃሹ ምንጭ የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ክፍተት እንደሆነ ተገምቷል፡፡ይኸዉም የተማሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ለስነልሳን የዕዉቀት ዘርፎች እኩል ትኩረት ያለመስጠት ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂል ላይ በቂ ልምምድ እንዳያደርጉ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡መምህራን በመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጽሀፉ ላይ ብቻ ተመርኩዘዉ ለጽህፈት በቂ ጊዜ ያለመስጠታቸዉም ሌላዉ ተጠቃሽ ነዉ፡፡

## 5.2. አስተያየት

በሽክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የተለያዩ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ የጥናቱ ዉጤት አመላክቷል፡፡ስህተቶቹን ጨርሶ መቅረፍ ባይቻልም በተወሰነ መልኩ ለመቀነስ የሚመለከታቸዉ ሁሉ ትኩረት ሰጥተዉ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የመፍትሄ መንገዶችን ቢወስዱ የተሻለ ይሆናል 

- ❖ መምህራን ተማሪዎቻቸዉ ስለ ታላሚዉ ቋንቋ ህግጋት በቂ ግንዛቤ ካለማግኘት ከሚፈጽሟቸዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖና የዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊታደጋቸዉ የሚችል ተደጋጋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን ቢያሰሩዋቸዉ፤

- ❖ መምህራን ተማሪዎቻቸዉን ሙሉ በሙሉ የመማሪያ መጽሐፍ ጥገኛ ብቻ ከሚያደርጉ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኙትን ሀሳብ በመፃፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንድያነቡ ቢያደርጓቸዉ፤

- ❖ መምህራን ተገቢዉን ትኩረት በመስጠት ተማሪዎቹ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የድምፆችን አሰዳደር፣የቃላትን፣የሀረጋትንና የዓረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ከተገቢ የሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ጭምር ባካተተ መልኩ በሰፊዉ ቢያጽፏቸዉ፤

- ❖ ጽህፈትን በሰፊዉ ለማለማመድ የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ምንም እንኳ ዉስን ቢሆንም መምህራን ተማሪዎቹ በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ልምምድ እንድያደርጉ መከታተል፤ከዚሁ ሂደት ጎን ለጎን መምህራን ተገቢዉን ግብረ መልስ የመስጠት ሚናን ቢወጡ ስህተቶችንና ምንጮቻቸዉን መቀነስ ይቻል ይሆናል፡፡

- ❖ በስህተት እርማት ወቅት መምህራን ጥቅል በሆነ የዐረፍተ ነገር ሥርዓት ላይ ብቻ ከሚወሰኑ በድምፆች አሰዳደር፣በቃላት፣በሀረጋትና በዐረፍተ ነገር አቀነጻጀት ላይ ከተገቢ የሥርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ጋር እያዋሄዱ የጽሁፋቸዉን የሀሳብ ጥንካሬ፣የመልዕክት ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀት እና የቃላት ግልጸት ጭምር አጽንኦት ቢያደርጉ ስህተቶችንና ምንጮቻቸዉን መቀነስ ይቻል ይሆናል፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች

መሰረት ጣፋ፡፡ (2003) ፡፡ "በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮሚኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ባየ ይማም ፡፡ (1987) ፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

ተገኝ አህመድ፡፡(2000)፡፡‹‹አፋቸዉን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች ትንተና፡፡››አርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (1970) ፡፡ "የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ከ7-12ኛ ክፍል፡፡" ስርዓተ ትምህርት እና ሱፐርቪዥን መምሪያ በአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፣ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)

ግርማ ሀይሉ፡፡ (2000) ፡፡‹‹በጌዲኦኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)

የአምላክስራ ህይወት፡፡ (2008) ፡፡ "የአማርኛ አፈፊት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት"፡፡ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2004) ፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Ap’ari Bac'uri .(2000). Shekigna Amharic English shekigna Dictionary.Addis Ababa; Commercial Printing Enterprise.

Byrne, D. (1990). Teaching Writing Skills. London:Longman.

Brown, H.D. (1994). Principles of language learning and teaching. New Jersey: Prentice Hall.Cambridge University press.

Corder, S. (1967). “The significance of earner’s Error.” IRAL. 12, 1፡ 11-127.

Dulay, H. (1982). Language Two. Oxford: Oxford University Press.

Ellis, R. (1989). Understanding Second Language Acquisitions. 5th ed. Oxford: Oxford University Press.

Jaksone, H. (1987). “The Value of Error Analysis and its Implications for Teaching and Therapy with Special Reference to Panjabi Learners.” In S.Abdurham (ed). Bilingualism and Bilingual.P100-111. Oxford:NFER-NELSON Publishing Company Limited.

James, C. (1991). Contrastive Analysis. 13th ed, New York: Longman Group UK Limited.

Little Wood, W.T (1986). Foreign and Second Language Learning. Language Acquisition Research and Its Implications for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Negara, E. A. (1985). “Non Contrastive Errors in African English: Types and significance.” IRAL. 16(1),1-77

Norrish, J. (1992). Language Learners and Their Errors. London: McMillan ublishers Ltd.

Nunan, D. (1999).Design tasks for the communicate class room, Cambridge University Press

Raimes, A. (1983). Techniques in Teaching writing. New York: Oxford University Press.

Richards, J.C. (ed). (1974). Error Analysis: Perspectives on Second Language Analysis.London and New York: Longman Group UK Limited.

Ur, P (1996). Course in Language Teaching :Practice and Theory Cambrige:Cambrige University Press.

# አባሪ አንድ

**በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ እንዲፅፉ የተሰጧቸው አማራጭ ርዕሶችና በራሳቸው መርጠው የፃፏቸው ርዕሶች**

*ትዕዛዝ አንድ*

**ከዚህ በታች ድርሰት ሊያፅፉ የሚችሉ የተለያዩ አማራጭ ርዕሶች ቀርበዋል፡፡ከእነዚህ ውስጥ የተሸለ ያጽፉናል የሚትሉትን በመምረጥ ከ 120-125 ባልበለጡ ቃላት ወይም ከ10-15 መስመር ባልበለጡ ጻፉ ፡፡**

**በአማራጭነት የቀረቡ ርዕሶች**

1ኛ.ኮሮናና ማህበራዊ ቀዉሱ

2ኛ.የትምህርት ጥቅም

3ኛ.የኑሮ ዉድነት

4ኛ.ሠላም

5ኛ.የቤተሰብ ፍቅር

6ኛ.እንሰት

**በራሳቸዉ ከመረጡ ርዕሶች**

ሀ.ኩረጃ

ለ.ድህነት

# የእንቀፀ አርእስት

መቅዳት የቃላት ብዛት = 85
የስህተት ብዛት = 34
የስህተት ዓይነቶች =
1:1=3
1:2=2
1:3=5
1:5=6
2:1=1
3:2=17
3:4=1

## 1:3 የኮሮና ወደም ኮቪድ 19

በአለማችን ላይ ቀና አስረ ና መድሀኒት የሌለው አደገ በሽታ ህገራችን እንትዳጂ፣ ሆኖ የትኛውንም ሀገሮን ያለፋሉ ኢትዮጵያ ይከላከውንም ትንሽ ተለቅንም ሙኒ ሰትንም ያለፋል ሀገሮችንና አለማችንን እሩ ያስያዘ ኮቪድ 19 የተባለው አደገ በሽታ የአለማችን ተደአሶች ያለውቁ ተመርምረም ያለተደፊሰ በለው እደለሙደ በለት የሆኑ የተከሰበ ኮሮና ሕገለሰ ወረም ኮቪድ 19 ተብሎ ይታወቃል

በወቀት ገበታ ያንሳመን የንፅሕናን ኮለደን በተሀደማሞትን መሰና መማዛትን ተለንስፓት ታዘን ሰውን ከሰው ዘመደን ከዘመደ ገተን ከምሽን ለደጆን ከለገት እናተደን ከለጆች ሀገርን ከሀገር ሰውን ከለማች በሁዋ ሰው እንደ ያለቅ የገጠ ፍንጠን የያዘው ቀለለ አደመሰለቾ ኮቪድ 19

## አንቀጽ

### ርዕስ፡- የንግምኒሆርት ኗቅም

መጣር የተለዘ ለምን ኑሮ አስምሮ አልም ወመንም አለዴ ለዩጣል፡፡ የተማር ሰው ለሠገልት ለገም፡ ዴሪ ፈቃር፡ ለዘት ገዘ ኀገሮች ወዬጠም ወዴም ወዬፈገለፈ ዴጃገል፡፡ እንደ ሰው ለገር ለአገል ኀተማረ ወዴም ለአለምሮወ ምመጃመን ኀገር ዴርሰለወ ገርት ለጠም ተወርት ኀተማር ዴዴርሰል፡፡ ኀዴረሰ ለን ም አራርት ዴለመጠል፡ ለተለለችንም ዴለመጠል፡፡ ዩለተማሪና የተማሪ ለምን መዴረሻ ለር አመተን ለሩመዴዴር የተማረወ ኀለመንገሩ አመቃ አንዴለወ ምን አንዴተናገር ዩለመን መለዩች ዴጃገል፡፡

ከጠቅላላ የቃላት ብዛት = 59

የስህተት ብዛት = 30

የስህተት ዓይነቶች =

1.1 = 3
1.2 = 5
1.3 = 1
1.4 = 2
1.5 = 3
1.6 = 6

---

2.1 = 2
2.2 = 3
2.3 = 2

ሰንቆጲ የእንቁጲ ርዕስ ደብ ኳራ

ኳራጲ ኳራጲ በተወሰ ሰዓት የም ኳራጲ

ሰዉ: ሬሳን ተመዪና: አቋርጦ ⊙ ኳርሺ: የሰዉን እሰዉ ቀን ደብዮጲንጲ: ሬሳን ሰራተ መሸከጽሪ ሊያመጣጋን በጣም ተዐዐና ባለይሸርሰዉ: ኳራጲ ደብዮን: ሰዉ ኳራጲን መቆጠ: ሬሳን ቶሎ ህገርን ተመዉ ሰለ ዐጥቶል: ክዘኑ: ኳራጲን መቶም አለብን ⊙ እንዷ: ሰዉ ሬሳን: ቶሎ እበ ሰንብ: ሬሳን ሰሬሳ ሰያ ሰተጸሪ ነው:: ኳራጲን: ሳንም ሠርቶ ሰቶ እኔ ሰመጣ ⊙ ሰንብ: ህገሮችን: ያሰባስ: ወሬም: ያጠፉ ኳራጲ ነው:: እሰኳሬጲ: ጲሳም: ሬሳን: ተመዪና ሰዎጲርስት ሰሀጉት ሰርሱ ሰጆ ወሰ ደሬት አሰቡ: ሰሞን ደተገሱ: የሰዉን የም ፈሰጠ: ሬሳን እየተመለመን ም: ኳራጲን እንደቀዩም ⊙


በተቃላለ የቃላት ብዛት = 69


የስህተት ብዛት = 23

የስህተት ዝርዝር =

1.1 = 2
1.2 = 1
1.3 = 2
1.4 1
1.5 = 14
3.1 = 2
3.2 = 3
3.3 = 1
3.4 = 3
3.6 = 3

4


ጠቅላላ የቃላት ብዛት = 68
የስህተት ብዛት = 33
የስህተት ዓይነቶች =
1.2 = 3
1.3 = 2
1.4 = 8
1.5 = 9
1.6 = 4
2.2 = 4
2.3 = 1
3.2 = 8
3.1 = 3
3.3 = 2
92


= 88
= 30
1.1 = 4
1.2 = 4
1.3 = 2
1.4 = 1
1.5 = 15
2.1 = 1
2.2 = 1
2.4 = 1
3.2 = 2
3.6 = 2
3.1 = 1
3.4 = 2
3.5 = 1
91


19/6/2013 G

[illegible]

# ኮሮና ቫይረስ

በአከባቢያችን ዶ/ር የኮሮና በሽታ ገዘ ለዓመታት
በዓለም ላይ ቀይ ቸግር ሰዎችን እየገዛ ያለው እንዱ
የኮሮና በሽታ ነው። ይህ የኮሮና በሽታ በዚህ ዘመን በዓለም
ላይ አለም ቸግር እንደፈጠረ መሆን በተከሰተ ዘገዳ
በተከሰተ ነገሮችን እየመጣን እንደሆን ነው። እንደሚ
ታውቀው፡ በተከሰተን፤ በሊያም እና በአይ የዓለም
ሁኔታ እንዳየን መሆኑን በሰፊው ስሞች ዘገቡ።
ይህ የኮሮና በሽታ ከሚያስከትለው እየከሰመን እየተጠጋ
ን ነበር። አሁንም ከሆነ ይህ የኮሮና በሽታ
እየቀጠለ እንደሆነ ደግሞ በፊርሃቻን በአጋጣሚ ወደ
ኋላ። ምክንያቱም ከዚህ በፊት ከተማዎችን
ገበያ ከዳይ ሰዎችን ወደ ቤት እየመጡና
ከገበያ ወደ ቤት ወደ ቤት እየመከሩን ስለዚህ
ለዚህ የኮሮና በሽታ ቀውስ ተጋላጮች እንሆናለን።

የተቃላሉ ቃላት ብዛት = ፳፰
የስህተት ብዛት = 15
የስህተት ዓይነቶች =
1.1 = 3
1.2 = 1
1.3 = 6
1.4 = 4
1.5 = 7
3.2 = 2
3.6 = 1



አንቀጽ
ርዕስ ጽህፈት
ለተጻፈ የቃላት ብዛት = 52
የስህተት ብዛት 13
የስህተት ዓይነቶች
1.1 = 2
1.2 = 7
1.5 = 1
3.1 = 2
3.3 - 1
3.6 = 1
94

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

### በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ዉድ ተማሪዎች

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀዉ በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና ለማጥናት ለተጀመረዉ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነዉ፡፡

ከጥናቱ የሚገኘዉ ዉጠትም ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች ለመቆጣጠር እንደ መፍትሄ አቅጣጫ ሊወሰድ ይችላል፡፡ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ ተገቢዉን መልስ እንድትሰጡ በትህትና ትጠየቃላችሁ፡፡

መጠይቁን ለመሙላት ለሚታደርጉት ቀና ትብብር ትመሰገናላችሁ!

**አጠቃላይ መረጃ**

1.በመጠይቁ ላይ ስምና ክፍል አይፃፍም፤

2.መጠይቁን በሌላ ሰዉ ማስሞላት አይቻልም፡፡

## ሠንጠረዥ 7 የመማር ማስተማር ሂደትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት በተመለከተ ከተማሪዎች የቀረቡ ምላሾች

| ተ.ቁ | | በጣም | ከፍተኛ | ከፍ | ተኛ | መካ | ከለኛ | ዝ | ቅተኛ | በጣም | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ መፅሀፉ ለድርሰት ፅሁፈት ክንዉን ትኩረት ስለመስጠቱ | | | | | | | | | | |
| 2. | መምህራን በክፍልና በተለያዩ አጋጣሚዎች ፅሁፈትን የማለማመዱ ሂደት | | | | | | | | | | |
| 3. | መምህራን የአማርኛን ትምህርት ዉብ፣ማራኪ ናአሳታፊ አድርጎ የማቅረባቸዉ ስልት | | | | | | | | | | |
| 4. | መምህራንስለ ድምፆች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዐረፍተነገሮች አቀነጃጀት ትኩረት ሰጥተዉ ማፃፍ | | | | | | | | | | |
| 5. | መምህራን ፅሁፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ብቻ የተገደቡ ይመስላሉ | | | | | | | | | | |
| 6. | መምህራን ከመማሪያ መፅሀፉ ይዘቶች በተጨማሪ ከመፅሄቶች ከመፃህፍት ከተሌቪዥንና ሬዲዮ መረጃ ሰብስባችሁ በፅሁፍ እንድታቀርቡ ማድረጋቸዉ ሂደት | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7. | መምህራችሁ የሚመቻችሁን ርዕሶች መርጣችሁ ድርሰት እንድትፅፉ የመከታተሉ ሂደት | | | | | | | | | | |
| 8. | የመምህራን የመልመጃ አስተራረም ይዘት በድምፆች፣በቃላት፣በመልዕክት ቅደም ተከተላዊ አቀነጃጀት፣በቃላት ግልፀትና ሀሳብ ጥንካሬ ላይ ትኩረት ስለመስጠቱ በተመለከተ | | | | | | | | | | |
| 9. | አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለህ ያለህ /ሽ ፍላጎት | | | | | | | | | | |
| | የአፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ልብህ/ሽ እንድትጠቀም/ሚ ያሳደረዉ ተፅዕኖ | | | | | | | | | | |

አማራጮች 1.በጣም ከፍተኛ 5.በጣም ከፍተኛ

2.ከፍተኛ

3.መካከለኛ

4.ዝቅተኛ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## በመምህራን የሚሞላ ቃለ መጠይቅ

## የተከበራችሁ መምህራን

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀዉ በሸካ ዞን የኪ ወረዳ በኩቢጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሸክኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና ለማጥናት ለተጀመረዉ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነዉ፡፡

ከጥናቱ የሚገኘዉ ዉጤትም ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸዉን ስህተቶች ለመቆጣጠር እንደ መፍትሄ አቅጣጫ ሊወሰድ ይችላል፡፡ስለዚህ መጠይቁን በጥሞና አንብበዉ ተገቢዉን መልስ ለመሙላት ለሚያደርጉት ቀና ትብብርዎ በቅድሚያ ይመሰገናሉ፡፡

**አጠቃላይ መረጃ**

**ፆታ** -----------------------------

አፍ የፈቱበት ቋንቋ-------------------------------

የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ---------------------------------

አማርኛን በማስተማር ያለዎት የስራ ልምድ-------------------

የመምህራን ቃለ መጠይቅ

1.የመማሪያ መጽሀፉ ለጽህፈት ክሂል ምን ያህል ትኩረት ይሰጣል?

2.ተማሪዎችዎን በተለያዩ አጋጣሚዎች ጽህፈትን በምን መልኩ ያለማምዷቸዋል?

3.የአማርኛን ትምህርት አሳታፊ፣ዉብና ማራኪ አድርጎ ለማቅረብ ምን ዓይነት ስልቶች ይጠቀማሉ?

4.ስለ ድምጾች፣ቃላት፣ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች አቀነጃጀት በምን መልኩ ትኩረት ሰጥተዉ ያጽፏቸዋል?

5.ጽህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት የትምህርት ይዘት ሙሉ በሙሉ በመማሪያ መጽሀፉ የተገደበ ነዉ? ወይስ ምን ዓይነት አማራጮች ይጠቀማሉ?

6.ተማሪዎች በጽሁፍ ሀሳባቸዉን ሲገልጹ ለሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች መንስኤ ናቸዉ ተብለዉ የሚገምታቸዉን ምክንያቶች ቢዘረዝሩ፤

7.የመልመጃ አስተራረም ይዘትዎ በድምጾች፣በቃላት፣በሀረጋትና ዓረፍተነገሮች አቀነጃጀት፣በቃላት ግልጸት፣ሀሳብ ጥንካሬ ወዘተ ላይ ምን ያህል ትኩረት ያደርጋሉ?

8.ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸዉ ፍላጎት በትምህርቱ ሂደት በምን መልኩ ይንጸባረቃሉ?

9.የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ልብ እንዳይጠቀሙ ያሳደረዉ ተጽዕኖ ይኖራል?በምን መልኩስ ይገለጻል?